
# 10. ተግባራዊው ገጽታ - ሙስሊሞችን በወንጌል ለመድረስ

## ዝግጅትና ልምምድ

ሙስሊሞችን በወንጌል ለመድረስ ስንሻ ማሟላት የሚገቡን ሦስት ነጥቦች አሉ። በበርጩማ ሦስት እግሮች ልመስላቸው እወዳለሁ። አንዱ የበርጩማ እግር ቢሰበር የተቀመጠበት ሰው መሬት ይወድቃል። እነዚህ ሦስቱ ምርኩዞችም: -



- መንፈሳዊነት
- እውቀት
- ልምድ ናቸው።

አንዱ የአንዱ መተኪያ ሊሆን አይችልም። ስለ እውቀት፥ መረዳትና ጸሎት በመጠኑም ቢሆን የተመለከትን ስለ ሆን አሁን ደግሞ ስለ ልምድ እናያለን።

በእናቱ ሆድ ውስጥ ሁሉን ተምሮና ተለማምዶ የሚመጣ ማንም የለም። ልምድ በመሥራት ይገኛል። የክርስቶስን ወንጌል ለመመስከር የተነሣውም ሰው ሲጀምር ያለ ልምድ ይሆንና በኋላ ግን ይካነዋል። ስለዚህም ልናደርግ የሚገባንን አሁኑኑ እንጀምር።

በሌላ በኩል ደግሞ ለሁሉም ነገር በቅድሚያ መዘጋጀቱ እጅግ ይጠቅማል። አለዚያ አደገኛ ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል። ዝግጅት ስንልም በዚህ ልዩ የወንጌል አገልግሎት ምክንያት ስለምንደርሳቸው ሰዎችና አቋማቸው በሚገባ ማወቅ ማለት ነው። እነዚህን ማስታወሻዎች ስታጠና፥ እድል አጋጥሞህ ስለ ጉዳዩ ሥልጠና ስትወስድ፥ ራስን ለዚህ አገልግሎት እያዘጋጀህ መሆኑን አትርሳ።

«ለሙስሊሞች ከመመስከሬ በፊት ስለ እስልምና ምን ያህል እውቀት ሊኖረኝ ይገባል?» ማለትህ አይቀርም። ነገር ግን ሙሉ በሙሉ ባታስታውሳቸው እንኳን እነዚህን ማስታወሻዎች በደንብ ከአጠናህ

ደኅና ተዘጋጅተሃል ማለት ነው። በተጨማሪም ደግሞ ማንኛውም ችግር ቢያጋጥምህ ለእኛ መጻፍ እንደምትችል አትዘንጋ። እናም ቆፍጠን በልና አእምሮህን አንቅተህ ሥራህን ቀጥል!

እንዲያም ሆኖ ታዲያ «ጌታ ሆይ፥ እኔ ማን ነኝ?» «ለዚህ የበቃሁ ነኝን?» ብሎ መጠየቅ የትሑት አገልጋይ መለያ ነው።

ይህንኑ ጥያቄ ሙሴም ጠይቆ ነበር (ዘጸአት 3፡11)፤ ኢሳይያስም እንዲሁ (ኢሳይያስ 6፡5)። ሁለቱም ለእግዚአብሔር ታማኝ አገልጋይ ሆነዋል። ኤርምያስም እግዚአብሔር በግልጽ እስከሚመልስለት ድረስ፥ አለመቻሉን እየጠቀሰ ተከራክሯል (ኤርምያስ 1፡6)። ጳውሎስም «ለዚህም ነገር የሚበቃ ማነው?» ሲል ጠይቋል (2ኛ ቆሮንቶስ 2፡16)። የተሰጠው መልስ ግን፡-

> «ብቃታችን ከእግዚአብሔር ነው እንጂ፥ በገዛ እጃችን እንደሚሆን አንዳችን እንኳን ልናስብ ራሳችን የበቃን አይደለንም» የሚል ነው (2ኛ ቆሮንቶስ 3፡5)።

ማንም ሰው ቢሆን የእግዚአብሔርን ሥራ ለመሥራት በቂ እውቀት፥ ልምምድ ወይም መንፈሳዊነት የለውም። እኔ ያለፍሁበትን ልንገራችሁ፤ ሙስሊሞችን በግል ጉብኝት ሳገለግል ብዙ ዓመት አሳልፌአለሁ፤ ብዙ ልምድ አለኝ ማለት ነው። ግን አሁንም እንኳን ወደ አንድ ሙስሊም ቤት ገብቼ ለመመስከር ገና በሩን ሳንኳኳ ብርክ-ብርክ ይለኛል። «ምን ይሉኝ ይሆን? ትኩረታቸውን እንዴት ለመሳብ እችላለሁ? እንዲያው ያዳምጡኝ ይሆን?» እላለሁ። ያም ሆነ ይህ ብቃታችን ከእግዚአብሔር የተነሣ ነው፤ የሰዎችንም ልብ የሚያዘጋጀውም ጌታ መንፈስ ቅዱስ ነው።

## ውይይትን ስንጀምር


ወንጌልን ለሙስሊም ለመመስከር ከመጀመራችን በፊት ምናልባት ሊከተሉ የሚችሉ አደጋዎች ካሉ፥ በጥንቃቄ ማስተዋል አለብን።

## ሀ. ለሙስሊሞች ስንመሰክር ቁርዓንን እንጠቀማለን?

አብዛኛውን ጊዜ መጠቀም የለብንም። የምንጠቀም ከሆነ ቁርዓንን ሆን ብለን ለማጣጣል ብለን ያደረግነው ይመስላቸዋልና፤ ውይይቱን

ከመቀጠል ይልቅ ለአካባቢው ኢማም ወይንም ሼክ ሄደው መናገርን ይመርጣሉ። እንዲያውም አብዛኛዎቹ ሙስሊሞች ቁርዓንን ይዘህ ስታነጋግራቸው ጥርጣሬ ያድርባቸዋል፤ ምናልባትም ከሙስሊሙ ጋር የመሠረትኸው ወዳጅነትም ሊበላሽ ይችላል።

የተለየ ሁኔታ ሲገጥመውና መስካሪው ጠለቅ ያለ የቁርዓን እውቀት ካለው ሁኔታው ሌላ ሊሆን ይችላል። ቁርዓንን ከተጠቀምን ለሙስሊሙ እንደ ትክክለኛ ምንጭ እንደ እግዚአብሔር ቃል የምንጠቅስ እንዳይመስለው መጠንቀቅ አለብን። ለዚህ መፍትሔው «ሙስሊም እንደ መሆንህ ይህንና ያንን ታምናለህ . . .» እያሉ ማነጋገሩ ነው።




ውይይቱ እየሰፋ ሲሄድ፥ የቁርዓንና የመጽሐፍ ቅዱስ ልዩነቶች፥ የቁርዓንን ድክመቶች መግለጽ አለባቸው። ያን ጊዜ ሙስሊሙ እምነቱን መጠራጠር ይጀምራል። ይህ ካልሆነ፥ ብዙውን ጊዜ ሌላ የተሻለና አስተማማኝ መረጃ ወዳለው ነገር ለመሄድም አይወስንም።

## ለ. እስልምናን ማጥቃት አለብን?

ለአንድ ሙስሊም ቅዱስ በሆነው ነገር ላይ ጥቃት መሰንዘር ማለት እንዲያው በአጠቃላይ አነጋገር አስጸያፊ ነገር ነው። ይሁን እንጂ ሙስሊሙ እስልምና የዘላለም ሕይወት ሊያወርሰው እንደማይችል ማወቅ አለበት። የአላህ ራእይ ነው ብሎ የሚታመንበትም ነገር ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ሲነጻጸር ብዙ ነቀፌታ እንዳለበት ማወቅ አለበት። ቁርዓን መለኮታዊ ምንጭ እንዳለው አንድም ማስረጃ ማቅረብ እንደማይቻል ሙስሊሙ መረዳት ይገባዋል።

የመጽሐፍ ቅዱስ እውነታን ስናስተላልፍ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ቁርዓን ከአብርሃም፥ ከይስሐቅና ከያዕቆብ አምላክ

አልመጣም፤ መሐመድም እውነተኛ ነቢይ አይደለም፤ እስልምናም ውሸት ነው ማለታችን ነው። አባባሉ ግን ሙስሊሞችን እጅግ ያስከፋቸዋልና ምናልባት ምስክርነታችን ከዳር እንዳይዘልቅ በሩን ይዘጋብን ይሆናል። ይሁን እንጂ ይህንን መልእክት ማስተላለፍ ግዴታችን ነው። ያንኑን ለማስተላለፍ ጥበብ፥ ዘዴና ፍቅር አስፈላጊዎች ናቸው።

በጣም ከማከብረው ከአንድ ሙስሊም ጋር ያደረግሁትን ውይይት ምን ጊዜም አልረሳውም። ውይይታችን ወደ ግጭት ሊያመራ በደረሰበት አንድ ሰዓት ላይ፥ ልነግረው የፈለግሁት ነገር እንደሚጎዳው ገለጽሁለት። እርሱም «የምትናገረው ነገር አስፈላጊ ከሆነ ተናገረው» አለኝ። እኔም ጀርባውን ቸብ አደረግሁና «አንተን ቅር ማሰኘት ለእኔም እኮ ሐዘን ነው። የምናገረው እውነተኛው ነገር ግልጽ እንዲሆን ብቻ ነው» አልሁት። ስሜቱን እንደ ጎዳሁት እርግጠኛ ነኝ፤ ነገር ግን ከአቀራረቤ የተነሣ ሊያደምጠኝ ቻለ፤ ይህ እውነት በግንኙነታችን ውስጥ አሉታዊ ገጽታ አላሳየም።

## ሐ. «ስለ መሐመድ ምን ታስባለህ?» ለሚል ጥያቄ የምንሰጠው መልስ

«ስለ እስልምና ወይም ስለ መሐመድ ምን ታስባለህ?» ተብለህ ፊት ለፊት ብትጠየቅ ምን ትመልሳለህ? እኔ በበኩሌ ለእንዲህ ያለው ጥያቄ ቀጣዩን ምላሽ በመስጠቴ ያጋጠመኝ ችግር አልነበረም፡- «እኔ ሕይወቴን ለጌታ አሳልፌ የሰጠሁ የተለወጥሁ ክርስቲያን ነኝ። እስልምና እውነተኛ የሕይወት መንገድ መሆኑን፥ እግዚአብሔር ገልጦልኝ ቢሆን በእርግጥ ክርስቲያን መሆን ባልቻልኩ ነበር። እስከ አሁን ድረስ ይኸው ማንም ሊያሳምነኝ አልቻለም። እኛ በመጽሐፍ ቅዱስ እናምናለን። መጽሐፍ ቅዱሳችንም ትንቢቱም በፍጻሜ ያልተረጋገጠ ማንኛውንም መልእክት እንዳንቀበል ያስጠነቅቀናል። (ዘዳግም 18፡21-22፤ ዘካርያስ 4፡9፤ ኢሳይያስ 41፡21፤ 44፡7፥ 26፤ አሞጽ 3፡7፤ ኤርምያስ 28፡9፤ ዘዳግም 13፡1-4)። አንድ ምሳሌ ልስጥህ» እላለሁ። ከዚያም በመቀጠል ስለ ጌታ ኢየሱስ መምጣት/መወለድ፥ በምድርም ላይ ሊያደርግ ስላለው ነገርና ስለ አሟሟቱ በብሉይ ኪዳን

የተተነበዩትን ትንቢቶች እናሳያቸዋለን። አያይዘንም ደግሞ ቁርዓን የኢየሱስ ክርስቶስን መምጣት፥ መጥቶም ሊከፍል ያለውን የኃጢአታችንን ዕዳ፥ እኛም ከእግዚአብሔር ጋር ለማስታረቅ በመስቀል ላይ የዋለበትን ዋና ጉዳይ መቃረኑን እናሳየዋለን። እናም በምርጫ አጣብቂኝ ውስጥ ታስገባዋለህ። እንዲህ ስትል፥ የትኛውን እንድመርጥ ይጠበቅብኛል? ብዙ የእግዚአብሔር ሰዎች ለብዙ መቶ ዓመታት የተነበዩለትን፥ የተናገሩለትን እውነትና በታላቅ ጥንቃቄ በአራት የተለያዩ የዓይን ምስክሮች የተመዘገበውን ወንጌል፥ በታሪክና በከርሰ ምድር ምርመራ (በአርኪዮሎጂ) የተረጋገጠውን እውነት እንድመርጥ? ወይስ ከ600 ዓመታት በኋላ በአንድ ሰው የተጻፈውን ለዚያውም አንድም የተፈጸመ ትንቢት ያልያዘውን መጽሐፍ ቁርዓንን እንድመርጥ? እንዲህ በንጽጽር መልክ ስለ እምነታችን ምንነት እያወዳደሩ ለመወያየት መሞከሩ ውጤት አለው።

## መ. ስለ «ጌታ ኢየሱስ»ና ስለ «ነቢዩ መሐመድ» ስንነጋገር

እነዚህን መጠሪያዎች እንዴት እናዛምዳቸዋለን? «ጌታ ኢየሱስ» የአንድ ሙስሊም ጌታ ነውን? መሐመድስ የአንተ ነቢይ ነውን? በእነዚህ ጥያቄዎች ውስጥ መልሳቸውም ይገኛል። ክርስቲያኖች ስንጸልይ ወይንም ስለ እርሱ ስንናገር «ጌታ ኢየሱስ» ብለን እንጠራዋለን። ክርስቲያን ካልሆኑት ጋር ስንነጋገር ደግሞ «ኢየሱስ ክርስቶስ» ወይንም «መሢሑ ኢየሱስ» ብሎ መጥራቱ እጅግ በጣም ተስማሚ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ስለ መሐመድ ነቢይነት በበኩሌ አልጠቅስም። ምክንያቱም ቢያንስ ቢያንስ በመጽሐፍ ቅዱስ መመዘኛ ነቢይ አይደለም።

## ሠ. ክርስቲያንና ምዕራባዊው የኑሮ ፈሊጥ

ሙስሊሞች ብዙውን ጊዜ የክርስቲያኖችን የኑሮ ዘይቤ በመመልከት የክርስትናን እምነት ለመገምገም ይሞክራሉ። በእነርሱ ግምት ክርስቲያን ማለት ሙስሊም፥ አይሁድና አረመኔ ያልሆነ ማለት ነው። ሌላው በሙሉ ክርስቲያን ይመስላቸዋል። የምዕራቡ ዓለም የአኗኗር ፈሊጥ ልቅ ሥነ-ምግባር፥ ስካርና የፈራረሰ የቤተሰብ ሕይወት፥ ወዘተ የክርስትና

እምነት ውጤት ነው በማለት ደምድመዋል። ስለዚህም ክርስቲያን ማለት በእርግጥ የክርስቶስ ኢየሱስ ተከታይ መሆኑን በውል ማስረዳት ያስፈልጋል። እንዲሁም በሆሊዉድ ፊልም የሚታየው ሁሉ አብዛኛው ሥነ-ምግባራዊም ክርስቲያናዊም አለመሆኑን መግለጽ ያስፈልጋል።

ከዚህ ሌላ እምነታችን ሰው የሚያደርገውን ሁሉ «የተፈቀደ» ወይም «የተከለከለ» በሚል ዝርዝር የሚከፋፍል መዝገብ እንደ ሌለው መናገር አለብን። ለአንድ ሙስሊም መንግሥተ ሰማይን ለመውረስ የሚያበቃው «የአድርግና አታድርግ» ህግጋት መጽሐፍ በጣም አስፈላጊ ነው። ክርስቲያኖች ግን ለመዳን ብለው የሚደከሙበት የሚገዛቸውም ሕግ የለም። ነገር ግን ኃጢአታቸውን ለመክፈል በመስቀል ላይ ለዋለው ጌታቸው ክብር ሲሉ ፈቃዳቸውን ስለሚያስገዙ ትክክለኛውን ነገር ያደርጋሉ። በግብረ ገብ በኩል የየራሳችንን ውሳኔ እንድናደርግ አስፈላጊ ነው። በክርስቲያን ሁሉ ዘንድ ይህ ውሳኔ የተለያየ ሊሆን ይችላል። አንድ ዓይነት የአምልኮና የሕይወት ዘይቤ ለመፈጸም ግድ አልተጣለብንም። እንደ ግለሰብ በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ ስለምንኖር፥ አንድኛችን የሌሎችን ፎቶ ኮፒ ልንሆን አያስፈልገንም፤ እግዚአብሔር ዓላማ ኖሮት ነው ሁላችንን የተለያየን እንድንሆን የፈጠረን።

## ረ. ሃይማኖታዊ ክርክርን ማስወገድ አለብንን?

አያሌ ክርስቲያኖች ስለ መንፈሳዊ ጉዳዮች መከራከር አያስፈልግም ይሉናል። ጳውሎስ ግን እንዲህ አላለም፡-

> «ከግሪክ አገርም መጥተው ከነበሩት አይሁድ ጋር ይነጋገርና ይከራከር ነበር» (የሐዋርያት ሥራ 9፡29)። «ከእነርሱ ጋር ከመጻሕፍት እየጠቀሰ ይነጋገር ነበር» (የሐዋርያት ሥራ 17፡2)። «በምኩራብ ከአይሁድና እግዚአብሔርን ከሚያመልኩ ሰዎች ጋር በየቀኑም በገበያ ከሚያገኛቸው ጋር ይነጋገር ነበር» (የሐዋርያት ሥራ 17፡17)። «በየሰንበቱ ሁሉ በምኩራብ ይነጋገር ነበር .... ያስረዳ ነበር» (የሐዋርያት ሥራ 18፡4)። «ወደ ምኩራብም ገብቶ ከአይሁድ ጋር ይነጋገር ነበር» (የሐዋርያት ሥራ 18፡19)። «ስለ እግዚአብሔር መንግሥት እየተነጋገረና እያስረዳቸው ሦስት ወር ያህል በግልጥ ይናገር ነበር» (የሐዋርያት ሥራ 19፡8)።

በአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ «መነጋገር» የሚለው በግሪክ ቃል «ዲያሌጎማይ» ሲሆን ትርጉሙም መከራከር፥ በሌሎች አመለካከቶች መወያየት ማለት ነው። ይህም መልካም ነው። ነገር ግን ከሙስሊሞች ጋር ስለ እግዚአብሔርም ሆነ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ እያነሡ «እንካስላንቲያ» መፍጠሩን እንቃወማለን።

## የተለወጠው ሙስሊም - ጎዳናውን ሲያጠራ

### ሀ. ምስክርነትና መለወጥ

> «የላከኝ አብ ከሳበው በቀር ወደ እኔ ሊመጣ የሚችል የለም ...» (ዮሐንስ 6፡44)።

የክርስቶስን ወንጌል መመስከር እንጂ፥ መለወጥ የእኛ ፈንታ አይደለም። የእኛ ምስክርነት ዓላማ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን በሚያሳያቸው መንገድ ሕይወታቸውን ለእግዚአብሔር አደራ እንዲሰጡ ለመጋበዝ ነው። ሰውንም ለውሳኔ መገፋፋት ሥጋዊ ጥረት ማድረግ ነው። ነገር ግን ሰውየው በቂ የወንጌል መረዳት ካገኘ በኋላ ቁርጥ ውሳኔ እንዲያደርግ መጋበዝ ያስፈልጋል።

### ለ. መለወጥና የኢየሱስ ተከታይ መሆን

ሙስሊሞች እንኳ ክርስቶስን ለመቀበል ሊወስኑ እንደሚችሉ ተስፋ አድርጎ መጠባበቅ ተገቢ ነው። ይህ ደግሞ ቀስ በቀስ እንጂ በአንድ «የጅምላ ስብከት» (ክሩሴድ) ላይ እንደሚሆነው ግለሰቡ ቀደም ብሎ ሳያስብበት እንደሚደረግ ውሳኔ አይደለም። ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑንና ለኃጢአቱም መሞቱን ሙስሊሙ አምኖ ከተቀበለ ጀምሮ ለውጥ በውስጡ እያለፈ መሆኑን አጢን። የእግዚአብሔርን ጸጋ፥ ይኸውም የኃጢአቱን ይቅርታና አዲስ ሕይወትን ይቀበላል ማለት ነው። እምነቱ በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረታዊ ትምህርቶች ላይ የተደገፈ ይሁን እንጂ የሰው ደምብ የሆነውን ሥርዓት ለመፈጸም ለምንድነው የሚያስፈልገው? አንዳንድ መሠረታዊ ያልሆኑ ጥያቄዎች አሁንም እንኳን ሊኖሩት ይችላሉ። ነገር ግን እንደ ከባድ ጉዳይ ሳናደርግ በጊዜ ሂደት ውስጥ ሰው ከሚናገረው ይልቅ የእግዚአብሔር ቃል ጥያቄውን እንዲመልስለት መንፈስ ቅዱስ እንዲመራው ጸልይለት።

ሙስሊም ክርስቶስን እንደ አዳኙና እንደ ጌታው በመቀበል ውሳኔውን ከገለጸ በኋላ፥ የኢየሱስ ተከታይ መሆን ይገባዋል። ስለሆነም ከሁሉ አስቀድሞ መሠረታዊ በሆነ የክርስትና እምነት ላይ የሚያተኩሩ ትምህርቶች ማዘጋጀትና መስጠት እጅግ አስፈላጊ ነው። ትምህርቱ የሚሰጠው ግን በቤት ውስጥ ፕሮግራም ሲሆን፥ ከመደበኛ የቤተ ክርስቲያን ትምህርቶች አቀራረብ በተለየ ስልት ነው። ይህ ዋና ነጥብ ነውና መዘንጋት የለበትም። ሙስሊሙ በቆይታው ጊዜ ስለ እምነትና የእምነት ሥራዎች ወዘተ ይማራል፤ ከክርስትና ልዩ ልዩ ገጽታዎችና ልምምዶችም ጋር ይተዋወቃል። በዝማሬ ማምለክን ይለማመዳል። አስተዋይ የሆነ መምህር ለሙስሊሙ አዲስ የሆነውን ሁሉ በብዙ ጥንቃቄ ያስረዳዋል፤ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት እንዳላቸውም ያመለክተዋል።

የጥምቀት ትርጉም አዲሱን አማኝ በማይገፋፋ መንገድ መገለጽ አለበት። ይህ ለእርሱ ትልልቅ እርምጃ ይሆናል!

## ሐ. ጉዞ ከጌታ ኢየሱስ ጋር

ሙስሊሙ ውሳኔ ካደረገ በኋላ ያለ ምንም ማመንታት ተግባራችንን መቀጠል አለብን። አዲሱ አማኝ የሚደግፉት፥ የሚያግዙትና ምክር የሚለግሱት ክርስቲያን የቅርብ ወዳጆች ያስፈልጉታል። በቤቱ ውስጥ እንዴት መመላለስ አለበት? ጌታ ኢየሱስን እንደ ግል አዳኙ እንደ ተቀበለ ለቤተሰቡ እንዴት አድርጎ ቢነግራቸው ይሻላል? በቅዋሜና በስደት ጊዜ ምላሹ እንዴት መሆን አለበት? የአሣማ ሥጋ ቢበላ ይሻላል? ባይበላ? ፆም የመውሰድስ ነገር? የተለመዱትን የሰላት ሰዓታት እንዴት ነው ማሳለፍ የሚገባው? ለሚነሡ ጥያቄዎችና ችግሮች ሁሉ ፍቅርና ማስተዋል የተሞላበት ምክር መስጠት ያስፈልጋል።

ሙስሊሙ አዲስ በጀመረው ጉዞው እንዳይደናገር ላልተወሰነ ጊዜ የሚያካሄደው ወዳጅ ያሻዋል። በጸሎትና በእግዚአብሔር ቃል ትምህርት ድጋፍ መስጠት ተገቢ ነው። ድሮ የኖረበት የእስላም ዓለም ጠልቶታል፤ የተደገፈበት ሁሉ ፈርሶአል፤ ስለዚህ በአዲሱ የክርስትና ዓለም ውስጥ ተደላድሎ እንዲኖር መንገድን የሚያመለክተው ረዳት

ያስፈልገዋል። እርሱ ራሱ ለጌታው የተሰጠ ተከታይ እስከሚሆን ድረስ ክብካቤ፥ ቸርነትና ግብቡነት ሳይቋረጥ ሊሰጠው ይገባዋል።

## መ. አዲሱ አማኝና ቤተ ክርስቲያን

«ቤተ ክርስቲያናችን ወደ ክርስትና ለሚመጡ ሙስሊሞች እንደ ራሳቸው ቤት ትሁን።» በየቤተ ክርስቲያኑ ላሉ ምዕመናን ሁሉ የይለፍ ቃል መስጫ መሆን አለባት። አዲስ ክርስቲያኖች የሆኑትን ሙስሊሞች ወደ ቤተ ክርስቲያን ተቻኩሎ አለመውሰዱ ግን ይመረጣል። ያ ሰው ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄዶ በሚሰማውና በሚያየው ለመባረክ እንዲችል መወጣጫ ደረጃ (በቤት ውስጥ ኅብረት መቆየት) ያስፈልገዋል። ለመሆኑ በመስጊድ ውስጥ የተካሄደ «የጀምአ» (ዓርብ) አምልኮ ተካፍለህ ታውቃለህ? ምናልባት አልተካፈልህም ይሆናል። ከሆነም ደግሞ እንዴት ተሰቅቀህ እንዳሳለፍከ አትዘነጋውም። ብዙ ጥያቄዎችም አእምሮህን ያስጨንቁታል። አንድ ጊዜ ወደ ቤታችን በእንግድነት ለመጣ ሙስሊም የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ስለ ነበረብኝ የምሔድበት ጉዳይ እንዳለኝ ነገርሁት። ጉጉት ስላደረበትም አብሮኝ ቢሄድ ቅር ይለኝ እንደሆነ ጠየቀኝ። ቅር እንደማልሰኝ ነገርሁትና መጣ። ነገር ግን ከበስተኋላ ለመቀመጥ ፈለገ። በኋላም በጣም እንደ ተጨነቀና በማንኛው ጊዜ ከቤተ ክርስቲያኑ ወጥቶ ለመሸሽ ዝግጁ እንደ ነበር አጫውቶኛል።

ተግባቢ ሰዎች የሚካፈሉበት የቤት ውስጥ ቤተ ክርስቲያን ወይንም ከእስልምና የመጡትን ሰዎች ያቀፈ ኅብረት ጥሩ የመወጣጫ ደረጃ ሊሆን ይችላል። በዚያም ለጋው አማኝ ከአንዳንድ የበሰሉ ክርስቲያኖች ጋር በመሆን የመጽሐፍ ቅዱስን መሠረታዊ ትምህርቶች ለመቃኘት ያመቸዋል። የአምልኮ ሥነ-ሥርዓቶችን ቀስ በቀስ ይለምዳል። «የቤት ውስጥ ቤተ ክርስቲያኒቱ» ግን መደበኛ የወንጌል ስርጭት ማዕከል መሆን የለባትም። ይልቁንም፥ ሙስሊሙ ለማንና ለምን መወሰን እንዳለበት ጠቁመው።

## ሠ. አዲስ አማኝ ሲሰደድ

ወደ አዳኙ ኢየሱስ ፊቱን የአዞረ ሙስሊም ሁሉ እርግጥ ነው በቤተሰቡ፥ በጓደኞቹ፥ በሙስሊም «ኡማ» ወይንም ኅብረተሰብ ዘንድ ወዲያውኑ ይነቀፋል፥ ይገለላል። ስለዚህም ቤተ ክርስቲያን ወይም ሌሎች የአማኞች ኅብረቶች የአዲሱ ሕይወት ቤተሰብና ወዳጅ ዘመድ እንዲሆኑት ኃላፊነቱ ወድቆባቸዋል። ለጥቂት ሳምንታት ያህል ብቻ ሳይሆን፥ በእምነቱ ጠንክሮና በክርስቲያን ኅብረቶች መካከል ተደላድሎ እስኪቆም ልዩ ክብካቤ ያስፈልገዋል።

### ከሙስሊሞች ጋር ለሚኖሩን ግንኙነቶች ጠቃሚ መመሪያዎች

ለሙስሊሞች ያለን አቀራረብ ለሌሎች ሰዎች እንደምናደርገው የተለመደ ዓይነት ቢሆን በጣም የተሻለ ነው። እንቅፋቶችን ሁሉ አስወግደን ከሙስሊሞች ጋር አንድ ጊዜ ጓደኛ ከሆንን ወንጌልን ለመመስከር የሚኖረን ዕድል ሰፊ ነው። ሙስሊሞችም ሰዎች ናቸውና በሰው ውስጥ ያለው ስሜትና ፍላጎት ሁሉ በእነርሱም ውስጥ አለ። ፍጹም ተቀባይነትና ፍቅር (መውደድ)፥ በጥልቅ ውይይት ሀሳብን መካፈል ሙስሊሞች የሚፈልጓቸው ዋና ዋና ነገሮች ናቸው።

ቤተ ክርስቲያን በአካባቢዋ ያሉትን የሙስሊም ቤቶች ሁሉ በመጎብኘት የበለጠ በተቀናበረ መንገድ የምትሠራበትን መንገድ መቀየስ አለባት። ይህም የቤት-ለቤት የወንጌል አገልግሎትን በመጀመር ይሆናል። በቤት - ለቤት አገልግሎት ጊዜ አቀራረቡ የተለመደ ስለማይሆን፥ በቅድሚያ ራስን አስተዋውቆ የመጡበትን ምክንያት መናገር ያስፈልጋል፤ ቀጥሎም የሚኖርህ ምርጫ «በቀጥታና በተዘዋዋሪ» አቀራረብ መካከል ይሆናል። «የአለህበትን አካባቢ ሃይማኖታዊ ጉዳዮች ለማጥናት ጥረት እያደረግን ስለሆነ ለጥቂት ደቂቃዎች መጠይቃችንን እንድትመልስልን በትሕትና እንጠይቃለን» ብሎ መጀመር ይቻላል። በጥሩ ሁኔታ የተቀናበረ መጠይቅ ጥሩ ጥሩ ጥያቄዎችን ስለሚያስነሣ ወደ ውጤታማ ምስክርነት ይመራሃል። ነገር ግን በመጀመሪያ ከሙስሊም ቤተሰብ ጋር ግንኙነት መፍጠር፥ አለዚያም በቀጥታ ወደ ነጥቡ ማምራት ከሁለቱ የትኛው እንደሚሻል

መወሰን ይበጃል። በበኩሌ በብዙ ምክንያቶች የተነሣ የደረጃ በደረጃ ምስክርነትን አጥብቄ እደግፋለሁ።

ብዙ ልምድ የሌላቸው ክርስቲያኖች በተለይ ለሙስሊሞች በተዘጋጀ ሥነ-ጽሑፍ ይጠቀሙ ወይም ወደ ጥሩ የክርስቲያን ቪዲዮ ዝግጅት ይጋብዙ ይሆናል። ሌሎቹ ከፊተኞቹ የተሻለ ልምድ ያላቸው ደግሞ ዕለታዊ የቤተሰብ የጽሞና ጊዜን ለመጀመር አንድን መኖሪያ ቤት ይጎበኙ ይሆናል። ሙስሊሞች ዕለታዊ የጸሎት ጊዜያቸውን ሊጠቁሙን ይችላሉ። ነገር ግን ፍላጎታችን ሰላት ስለ መስገድ እንዳልሆነ መግለጽ ያሻል። ይልቁንም ጽሞናችን የእግዚአብሔርን ቃል መስማትንና በፈንታችንም ማንም በቅድሚያ ያልደነገገውን የግል ጸሎት ለመጸለይ መሆኑን ይፋ ማድረግ ነው። ሙስሊሞች ቁርዓንን እንደሚያነቡ ይመስላቸዋል። ነገር ግን «ቁርዓንን በየቀኑ ታነባለህ?» ብትሏቸው፥ «አይ፥ በየቀኑ እንኳን አይደለም» ይሏችኋል። አሁን ወደ መንፈሳዊ ውይይት ተገባ ማለት ነው።

በይበልጥ ደግሞ ቀጥተኛ የሆነው አቀራረብ «ዛሬ ብትሞት ምን እንደምትሆን፥ ምን እንደሚደርስብህ ታውቃለህ?» ወይንም «ከሞት በኋላ በእግዚአብሔር ፊት ስትቆም፥ እግዚአብሔር ወደ መንግሥተ ሰማይ እንድትገባ የሚፈቅድልህ ከምን የተነሣ ይመስልሃል?» እንዲህ ዓይነት አቀራረብ በእርግጥ ለመንፈሳዊ ውይይት በር መክፈቻ ነው። ፍቅር የበዛላቸው ክርስቲያኖች መዳረሻ የሚሆኑ ሌሎች ብዙ መንገዶችን ለማሰብ ይችላሉ።

ጥያቄዎችን መጠየቅ ውይይት ለመጀመር በጣም ጥሩ መንገድ ነው። አብዛኞቹ ሰዎች ከሁሉም በፊት ስለ ራሳቸው፥ ስለ ስሜታቸው፥ ስለ እምነታቸውና ስለ ሁኔታቸው እንዲናገሩ ሲጋበዙ ጥሩ ስሜት ይሰማቸዋል። በሚገባ ማድመጥም ደግሞ የጥሩ ውይይት ገጽታ ነው። ሌሎችን በመልእክታችን፥ ወይም በምስክርነታችን፥ ወይም በምናውቃቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ማደናቀር ግራ ማጋባት የበለጠውን እንዲከላከሉ ወይንም መልሰው እንዲቃወሙ መገፋፋት ሊሆን ይችላል። ጥያቄዎችንም በላይ በላይ ማከል ጥሩ አይደለም፤ መርማሪ ፖሊስ ያስመስላችኋል።

ጥያቄዎቻችን የተጀመረውን ውይይት ይበልጥ ለማዳበር የታሰበባቸው ሊሆኑ ይገባል። «በቀን አምስት ጊዜ እንደምትጸልዩ እሰማለሁ። ይህን የምታደርጉት ለምንድነው? ሰው ሁሉ ለምን በአንድ ዓይነት መንገድ ይጸልያል? ጸሎቱን 10000 ጊዜ ደጋግመህ ከአነበብኸው በኋላ፥ እንዴት እንደ እውነተኛ የአምልኮ ሥርዓት ሆኖ ይሰማሃል? ዝም ብሎ ልማድ ብቻ አይሆንብህምን?»

«መሥዋዕቶችን እንደምትሰዉ እሰማለሁ። የምትሠዉት እግዚአብሔር ለአብርሃም፥ ወይም ለሙሴ ባዘዘው ዓይነትና መንገድ፥ በዚያውም ዓይነት ዓላማ ነውን? መሥዋዕት ማቅረቡ ምን ፋይዳ አለው?»

«ሙስሊሞች እስልምናን የአብርሃም ሃይማኖት ነው ይላሉ። በምን መንገድ?»

«ለሐጂ ኡምራ ጉዞ ወደ መካ ሄደህ ታውቃለህ? እዚያ በመቶና በሺህ ከሚቆጠሩ ሌሎች ሙስሊሞች ጋር መሆን ምን ዓይነት ስሜት ያሳድራል? ይህ ብዙ ገንዘብ አይፈጅምን? በካባ ውስጥ ያለውን ጥቁር ድንጋይ ለምን ትስማላችሁ - ትሳለማላችሁስ? እኛ ይህንን የጣዖት አምልኮ ነው እንላለን። መሐመድ ለዐረቢያ አዲስ ሃይማኖትን በማስተማር ላይ እያለ፥ ለምን የጣዖት አምላኪዎችን ሥርዓት አላስወገደም?»

> በመሠረቱ እነዚህን ጥያቄዎች የሚጠይቅ ሰው የመጽሐፍ ቅዱስ መልሶቻቸውን ማወቅ አለበት! ጥያቄዎቹ መጨረሻ ላይሆናቸው ይችላል። ቢሆንም ያለ ዓላማና ግብ መጠየቅ የለባቸውም። ያን ጊዜ ሙስሊም ወዳጅህ ማሰብ፥ ማነጻጸርም ይጀምራል!

ለሙስሊሞች ወንጌልን ማድረስ እንዲሁ ውጤት አያስገኝም። ምናልባት «አቦ ለቀቅ አድርጉን!» ይሉን ይሆናል። ይህ የሚሆንበት አጋጣሚ ግን በጣም ጥቂት ነው። ለሙስሊሞቹ እየመለሱ ሳሉ ሌላ ጥያቄዎችን ያነሣሉ፤ ወይም እኛ ስንመልስ፥ «... እኛ ይህን በተለየ መንገድ እናየዋለን፤ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ጉዳዩ ... እንዲህ እንዲህ ይላል» በማለት የእግዚአብሔርን ቃል ማካፈል መልካም ነው።

ውይይቱን መምራት በጣም ጠቃሚ ነው። ሙስሊሞች ሊመልሱት የማይችሉት ጥያቄ ከመሰላቸው፥ የመጽሐፍ ቅዱስን አሳብ «ፉርሽ» ማድረግ የማይቻል መስሎ ከታያቸው፥ ርዕስ የመለወጫ ዘዴ አላቸው። መልሱን ለማድመጥ የማይፈልጉትን የማይረባ ጥያቄም ሊያነሡ ይችላሉ፤ ያኔ ግን የምንደርስበት ውሳኔ ከጉዳዩ ጋር ያልተያዘ እንኳን ቢሆን ውይይቱን በብቃት መምራት ያስፈልጋል።

ሙስሊሞች ጌታ ኢየሱስን ወይንም መጽሐፍ ቅዱስን እያንቋሸሹ ሲናገሩ ንዴት ሊቀሰቅስብን ይችላል፤ ግን አይሁን፤ በእርጋታና በራድ በሆነ ስሜት ውይይቱን መቀጠል ያስፈልጋል። መናደድ የሚሰጠው ፋይዳ የለም። ከቁጥጥር ውጭ በሆነ አተካራ ማንም ምንም አያተርፍም። እርግጥ ነው አንዳንድ የእስልምና ክርክሮች እልኃችንን ለማስጨረስ ተነጣጥረው የተዘጋጁ ናቸው። ቢሆንም ክርስቶስን ለመምሰል በመንፈስ ቅዱስ ኃይል መንፈሳችንን የምንገዛ ሆነን መገኘት ይገባናል።

ነጥባችንን በምሳሌ ማብራራት ትልቅ አስፈላጊነት አለው። ሁሉም ሰው ስውርና ረቂቅ የሆነን አሳብ በቀላሉ ሊረዳ አይችልም። በአንዳንድ ባህሎች የቋንቋ አጠቃቀሙ ምሳሌያዊ ወይንም ሥዕላዊ ነው። ማንኛውም ረቂቅ አሳብ፥ በተለይ በመንፈሳዊ ትምህርት አቀራረብ ምሳሌዎችን፥ ምልክቶችን፥ ታሪኮችን፥ ወዘተ በመጠቀም ሊጎላ ይችላል። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስም በጣም ተጠቅሞባቸዋል። እኛም ተመሳሳዩን ነገር እንድናደርግ ልንበረታታ ይገባል። (የተመረጡ ምሳሌዎች በመጨረሻው ላይ ታገኛለህ። ሌሎቹን ታውቅ ይሆናል፤ ጽፈህ አካፍለን።)

«ጥበብ፥ ግንዛቤና ማስተዋል» ሊረሱ የማይገባቸው የአንድ መስካሪ ባሕርያት መሆን አለባቸው። መጽሐፍ ቅዱስን በመመርኮዝ መንፈሳዊ ውይይት እያካሄድን ሳለ ቤተሰቡን ወይንም ጓደኛውን ለመጠየቅ በመጣ ሰው በሩ ቢንኳኳ የቤቱን ባለቤት ላለማስጨነቅ ስንል አርዕስቱን ለጊዜው በመለወጥ መጽሐፍ ቅዱሱን በኪሳችን መከተት ያስፈልጋል። ሙስሊሞች ሌሎች ሙስሊሞችን ስለሚፈሩ ውይይቱን መለወጣችን ያስደስታቸዋል።

ቅዱሳት መጻሕፍትን በትልቅ አክብሮት ይይዛሉ። ቁርዓን ምናልባት ሁልጊዜም በጨርቅ ተለብዶ በክፍሉ ባለው መደርደሪያ እከፍተኛው ቦታ ላይ ተቀምጦ ይሆናል። ቅዱሳት መጻሕፍትን ወለል ላይ ማስቀመጥ እንደ ትልቅ ነውር ይቆጠራል። እኛም መጽሐፍ ቅዱሳችንን እንዴት መያዝ እንደሚገባን ያስገነዝበናል።

የምትናገረውን ነገር ሁልጊዜም በመረጃ ለማጠናከር ተዘጋጅ! የግላችን የሆኑት አመለካከቶችና አሳቦች አይጠቅሙም። (ያላቸው ጠቀሜታ በጣም ጥቂት ነው።) የማሳመኛ ዓረፍተ ነገሮችን የምንጠቀመው ከመጽሐፍ ቅዱስ ይሁን፤ ከታሪክ ወይም ከእስልምና ስንወስድ ግልጽ ማድረጋችንን ማረጋገጥ አለብን። ለዚህም አስፈላጊ የማጣቀሻ ክፍሎችን ማቅረብ ይኖርብናል። በእርግጥ ሁልጊዜ ወዲያውኑ ማቅረብ የማይቻል ይሆናል፤ ነገር ግን በሚቀጥለው ቀጠሮ ለማቅረብ መሞከር ነው። ነጥቦችህ ትክክለኞች መሆናቸውን ለማረጋገጥ ሙስሊም ጓደኛህም ይህን እንደሚያደርገው ጠብቅ። በተለይ እኛ ራሳችን ስለ እስልምና እምነት ካወቅን፥ ይህንን ለማድረግ ያስቸግረዋል።

የወንድና የሴት ግንኙነት በሙስሊም ኅብረተሰብ ዘንድ እጅግ ጥብቅ ነው፤ እግዚአብሔር በሁሉም ማኅበራዊ ግንኙነታችን በበጎ ሥነ ምግባር እንድንመላለስ እንደሚፈልግብን አትዘንጋ። ለነገሩ እንኳን ይህ ለእኛ አዲስ አይደለም። በእስልምና ነገሮች ሁሉ በሕግ የተደነገጉ ሲሆኑ፥ በተለይም በተቃራኒ ጾታዎች ግንኙነት ላይ ተፈጻሚነት አለው። ስለዚህም የሃይማኖት ውይይት እንኳን ቢሆን፥ ብዙ ሰዎች ባሉበት ስፍራ ካልሆነ ወንድና ሴት ብቻ ሆኖ መሳተፍ ፈጽሞ አያስፈልግም። በብዙ የሙስሊም አገሮች ሴቶች ካልተሸፋፈኑ ሕዝብ ከተሰበሰበበት ቦታ እንዲደርሱ አይፈቀድላቸውም። ይህን ከአስተዋልን ወደ ሌላ ርዕስ ያመጣናል።

ልብስ፤ ሙስሊሞች የምዕራባውያንን፥ በተለይም የሴቶችን አለባበስ የማይገባ፥ እንዲያውም ነውር አድርገው ይቆጥራሉ። አባባላቸው ደግሞ ስለ ሥነ-ምግባርና ትሕትና ባለን ግንዛቤ ላይ

የተመሠረተ ነው። ስለዚህም ሴት መስካሪ ለሙስሊሞች በሚስማማ መንገድ ብትለብስ ጥሩ ነው። ለምሳሌም ድሪያና መቀርሚያ።

<u>የአኗኗር ልማድ</u> እንደ አየባህሉ በጣም የተለያየ ነው። በሙስሊሞች ዘንድ ለምሳሌ ቀኝ እጅ የሚያገለግለው ለንጹህ ነገሮች ነው፤ ምግብ መብላት የሚቻለው በቀኝ እጅ ብቻ ነው። ግራ እጅ ደግሞ ንጹህ ላልሆኑ ነገሮች ማከናወኛ ነው። ስለዚህም በአድራጎታችን ምግባራቸውን እያቃለልን ቅሬታ እንዳንፈጥር መጠንቀቅ አለብን። በአንዳንድ ሙስሊሞች ዘንድ እግር አጣምሮ መቀመጥ ነውር ነው። ውሾች ርኩስ እንስሳት ተብለው ስለሚቆጠሩ መንካት አይፈቀድም። አስተዋይ መስካሪ ቅሬታ የሚፈጥሩ ምግባሮች ምን እንደሆኑ በብልሃት እየጠየቀ መረዳት ይችላል።

<u>እንግዳ አቀባበል</u> በምሥራቃውያን ዘንድ ትልቅ ግምት የሚሰጠው ጉዳይ ነውና ሊተኰርበት ይገባል። ግብዣ ሲቀርብ «እንቢ» ማለት ቅሬታን ሊያስከትል ይችላል። በሌላ በኩል ግን ሙስሊሞች የእኛን ግብዣ ለመቀበል እንደማይፈልጉ ማወቅ አለብን። ምክንያትም አላቸው፤ እርሱም «ሐራም» ማለትም እርም ወይም የረከሰ፥ የተከለከለ ነገር እንዳይወስዱ በመሥጋት ነው። ሙስሊሞች እንዲበሉ የተፈቀደላቸው «ሐላል» የሆነውን ብቻ ነው። ይህም ንጹሕ፥ የተፈቀደ ወይንም የተባረከ ማለት ነው። በሠለጠኑት አገሮች የሚገኙ ምግብ ቤቶች በዝግጅቶቻቸው ላይ የሐላል ምልክት ያደርጋሉ። ብዙውን ጊዜ ግን ንጹህ መሆን የሚያስፈልገው ሥጋ ስለሆነ፥ ከንጹህ እንስሳ የተገኘ መሆን አለበት። ዓሣማ ለሙስሊሞች አልተፈቀደም። ንጹሕ የሆነው እንስሳም ቢሆን በእስልምና ባህል መሠረት በጸሎት ተባርኮ መታረድ አለበት። ሙስሊም እንግዶች በሚጋበዙበት ጊዜ ሐላል ምግቦችን ማቅረብ የአክብሮት መግለጫ ነው።

## አጭር ማጠቃለያ

1. ሙስሊሞች የራሳቸው የሆነ ልዩ ጠባይ አላቸው። በአለባበስህና በሌላውም አካሄድህ ከሙስሊም ወዳጅህ ጋር ያለህ ግንኙነት እንዳይበላሽ ተጠንቀቅ። ግንኙነታችሁን ለማዳበር የተፈጥሮ ጥበብህን

ተጠቀም፤ ደግሞም ወዳጅህ የሚከፋበትን ነገር በግልጽ እንዲነግርህ በትሕትና ጠይቀው።

2. በትሕትና ለመስማትም ለመማርም የተዘጋጀህ ሁን። ስለ እምነታቸውም ሆነ ስለ ራሳቸው ከሙስሊሞች የምትማረው ብዙ ነው።

3. ከሙስሊሙ ጋር ለምታደርገው ግንኙነት ትኩረት ስጥ። የምንለያይበት ብዙ ነጥብ ቢኖርም እርስ በርስ ብንከባበር ግን ብዙ አብሮ መጓዝ እንችላለን።

4. መልካም እንግዳ ተቀባይ ሁን። ሙስሊሞች ሐላል ከተደረገው በቀር አይቀምሱምና ጥንቃቄ እንዳይጎድልህ። ምናልባትም በአንተ ቤት መመገብ አይፈልጉም ይሆናልና፤ ፈቃዳቸውን ጠይቃቸው፤ ለመስማማትም አማራጮችን መርምር።

5. ቀና ሁን። ወደ ቃል ድብድብ አትግባ። በእንካስላንቲያው አንድኛችሁ እስከምትረቱ አትጠብቅ። ወንጌሉን በፍቅርና በማስተዋል ለማካፈል ሞክር። እንደ ተረዱህ እርግጠኛ ሁን። ሃይማኖታዊ ጽንሰ - አሳቦችንና ቃላትን በሚገባ አስረዳ፤ አድማጭህም የተናገርኸው ሁሉ ገብቶት እንደ ሆነ አረጋግጥ።

6. ከልክ በላይ አትስማማቸው። ደግመህ ደጋግመህ ሙስሊሙ እውነትን እንዲፈትናት አበረታታው።

7. ሙስሊሞች የምንናገረውን ሁሉ ለመቃወም ከቃላችን ኋላ ያደባሉ ብለን አናስብ። የተሻለ የመገናኛ መንገድም እንቀይስ። ውይይቱን ሁልጊዜ መምራት ያለብን እኛው ነን።

8. እስልምናን፥ መሐመድን፥ ቁርዓንን ወይም አላህን በንግግርህ አትውጋ። እነዚህ ሁሉ ለሙስሊሞች የተቀደሱ ናቸውና። ስለ እነርሱ ክፉ ወሬን ሊታገሡ ስለማይችሉ የተከፈተው በር እንዳይዘጋ ተጠንቀቅ።

9. ውሳኔን ለማፋጠን ተብሎ በቅድሚያ የተዘጋጀ የወንጌል ስርጭት ዘዴዎች አትጠቀም። ሰውዬው መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ኃጢአት የሚለው ሁሉ እውነት መሆኑን ካልተቀበለ፥ ሰው ኃጢአተኛ የሆነው ኃጢአትን ስለ ፈጸመ ሳይሆን፥ ሰው ኃጢአት የሚያደርገው ኃጢአተኛ ስለሆነ መሆኑን ካልተቀበለ (ሁለቱ ብዙ ልዩነት አላቸውና)፥ እግዚአብሔር መፍትሔ ካልሰጠው በቀር ሰው በዘላለም ሞት ፍርድ ሥር መሆኑን ካልተቀበለ፥ የእግዚአብሔርም ለደኅንነት የመረጠው መንገድ ስለ

ኃጢአታችን በመስቀል ላይ በሞተው በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል መሆኑን ካላመነ በስተቀር ከአንድ ሙስሊም የእምነት ውሳኔ አይጠበቅም።

10. በአጭር ጊዜ ውስጥ የምሥራችን ወንጌል ጠቅላላ ይዘት በጠቅላላው መናገር ተገቢ አይደለም። ለሙስሊም ደህና አድርገን ማስረዳት ኃላፊነታችን ነው፤ ለእርሱ እንግዳ የሆኑት ሃይማኖታዊ ቃላትና አባባሎች ከማብራሪያ ጋር መቅረብ አለባቸው። በተጨማሪም እንደ ዋዛ ረግጧቸው የማያልፋቸውን ብዙ ነጥቦች እንዲያሰላስል ጊዜ ማግኘት አለበት። ይኼ ነጥብ የጅምላ ስብከት (የአደባባይ ወንጌል ስርጭት) ለሙስሊሞች የማይጥም መሆኑን ያስገነዝብሃል። (ለጅምላ ስብከት የወሰኑ ሙስሊሞች ቁጥር እጅግ በጣም አናሳ መሆኑን ልምድ አስተምሮናል።)

11. ልብ በል! በሞትና በሕይወት፥ በጨለማና በብርሃን፥ በእግዚአብሔርና በሰይጣን መካከል በሚደረግ ፍልሚያ ውስጥ እንዳለህ ሁልጊዜም አስታውስ። ጥረትህ ሁሉ የሰመረ ቢመስልህ ወይም ባይመስልህ ሙስሊሙን ወደ አዳኙ የሚጠራውና የሚለውጠው መንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው። ስለዚህም በጸሎት መዋጋት የቅድሚያ ሥራህ ይሁን፤ እርሱ ከጥበብህም፥ ከመግባባት ችሎታህም በላይ ነውና።

# 11. ወደ ተግባራዊው እርምጃ

## ሙስሊሞችን እንዴት እንድረሳቸው?

ይህን ጥያቄ በሕያው እግዚአብሔር ፊት ስንጠይቅ እና ለታላቁ ተልዕኮ፥ በተለይም ስለ ሙስሊሞች ታዛዦችና ታማኞች መሆናችንን ቃል ብንገባ የጥያቄውን መልስ አገኘን ማለት ነበር።

በጥቂት ጊዜ በታላቁ የእግዚአብሔር የወይን እርሻ ላይ ከሁሉ አስቸጋሪ በሆነው ክፍል ውስጥ እየሠራህ እንደሆነ ትገነዘባለህ። ደግሞም ሥራውን በሚገባ ለማከናወን እግዚአብሔር እንደሚደግፍህና ለሥራው አስፈላጊ ሥጋዊና መንፈሳዊ ስጦታ ሊሰጥህ እንደሚችል በመተማመን በጸሎት ለመጠየቅ ትችላለህ።

እንግዲህ ሙስሊሞችን በወንጌል እንዴት እንድረሳቸው? ወዳሉበት በመሄድ ነው! አንድን ሙስሊም ወደ ቤተ ክርስቲያን በመጋበዝ

የሚገኘው ውጤት ትንሽ እንደሆነ አስቀድመን ተመልክተናል። በመጀመሪያ ደረጃ እነርሱ ወደ ቤተ ክርስቲያን ለመምጣት ፈቃደኛ አይሆኑም። በተጨማሪም የሚነገረውንና የሚደረገውን ለመረዳት ጭንቅ ይሆንባቸዋል። ደግሞም ጌታችን ያለው «ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ» ነው እንጂ «ዓለሙ ሁሉ ወደ ቤተ ክርስቲያን እስኪመጡ ጠብቁ» አይደለም።

## ዘዴ ቀይስ

ቤት ከመሥራትህ በፊት እቅድ ታወጣለህ። የክፍሎቹን ብዛት፥ ስፋታቸውን፥ ለሕንፃው የምትጠቀምባቸውን ቁሳቁሶች ዓይነት፥ የገንዘብ አቅምህን፥ ወዘተ ትገምታለህ። ሁሉም ከተሟላ በኋላ አናጢ እንዲሠራልህ ያስፈልግ እንደሆነ ወይንም አንተና ጓደኞችህ እንደምትሠሩ ውሳኔ ላይ ትደርሳለህ።

በተመሳሳይ መንገድ ለእስልምና የወንጌል አገልግሎት እቅድ ታወጣለህ። የሚገጥመን ችግር ተስፋ የሚያስቆርጥ ሳይሆን፥ የማሸነፍን ዘዴ እንድንፈልግ የሚያስነሣን ይሁን።

| ጉዳዩን ፊት ለፊት መጋፈጥ | መፍትሔ መሻት |
|---|---|
| - መደረግ ያለበት ምንድነው? በግሌ ልሠራው እችላለሁ? | ካልሆነስ ከእኔ ጋር እንዲሠራ ማንን ላግባባ እችላለሁ? |
| - ስለ ጉዳዩ ተጨማሪ መረጃ ወይንም ሥልጠና ያስፈልገኛልን? | እንዴትስ ላገኝ እችላለሁ? |
| - ቤተ ክርስቲያን ከእኔና ከአበሮቼ ጎን ትቆማለችን ትጸልይልናለችን? | ካልሆነስ የቤተ ክርስቲያንን ድጋፍ እንዴት ላገኝ እችላለሁ? |
| - ሥራው ከቤተ ክርስቲያንና ከአባሎችዋ ዐቅም በላይ ነውን? | ከየትኛዋ ቤተ ክርስቲያን ወይንም ድርጅት ጋር መተባበር እችላለሁ? |

በትንሹ መጀመር መልካም ቢሆንም፥ ሥራውን በተሟላ ሁኔታ ለማዳረስ ግን እቅድ መውጣት አለበት። በተቻለ መጠን ብዙ ክርስቲያኖችን በማሠልጠንና በማነቃቃት አገልግሎቱን ማስፋት ይቻላል። አገልግሎቱን የማሳደጊያ ሌላው ዘዴ ደግሞ በእውነት በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ በመሠረታዊ እምነታቸው አንድ የሆኑትን የተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት ማስተባበር ይሆናል። ስለ ሙስሊሞች በእርግጥ ማንኛውም ምዕመን መጸለይ አለበት። («ስለ እነዚህስ አይገድህምን?» የተሰኘ አነስተኛ መጽሐፍ በአድራሳችን ጠይቀህ ማግኘት ትችላለህ።)

ሙስሊሞችን በወንጌል ለመድረስ የምዕመናን ሁሉ ትኩረት ካልተጨመረበት በስተቀር፥ ሥራውን በስፋት ለማከናወን ውጤትንም ለማግኘት አስቸጋሪ ይሆናል።

አገልግሎቱን ለማስጀመር ሥልጠናም ለማግኘት ምናልባት ባለ ሙያ ያስፈልግህ ይሆናል። ካላገኘህ ጽፈህ ጠይቀን። ለሥልጠናው የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችንም ጠይቀህ መውሰድ ትችላለህ።

በተለይ ለሙስሊሞች የወንጌል ስርጭት የተዘጋጀ ሥነ ጽሑፍ ያስፈልግሃል፤ ነገር ግን በብዙ ጥንቃቄ መምረጥ አለብህ። መደበኛ በራሪ ጽሑፎችን አትጠቀም። ለሙስሊሞች ጣዕም አይስማሙምና።

ከአንተ ጋር ለመጸለይና ለመሥራት ራሳቸውን ለመስጠት የወደዱ ክርስቲያኖችን በማሰባሰብ እርምጃህን ጀምር። ከዚያም በጋራ አቅዱ፤ በጋራ ሠልጥኑ፤ በጋራ ዘዴ ቀይሱ።

ብዙ ዓይነት መንገዶችም ይታዩአችኋል:-

* ቤት-ለቤት ጉብኝት ማድረግ

* ወዳጅነት መመሥረት:- እምነትህን ከጓደኞችህ፥ ከጎረቤቶችህና አብረውህ ከሚሠሩት ጋር ለማካፈል ዓላማህ ይሆናል። ብዙ ሰዎች በዚህ ሥራ እንዲተባበሩህ ያስፈልጋል። (ለዚህ የተለየ ጽሑፍ አለን፤ ጠይቀህ ውሰድ።)

* የሥነ ጽሑፍ ስርጭት፡- በአንተ አካባቢ ንባብ ለሚያውቁት ሙስሊሞች ተስማሚ ሥነ ጽሑፍ ፈልግ፤ ወይም የራስህን እንድታወጣ እርዳታን ጠይቅ፤ ከዚያም በእያንዳንዱ ቤት አሰራጭ። መከታተልህን ግን አትተው።

* የቤትህ ውስጥ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት፡- ይህ በእነርሱም ቤት ሊሆን ይችላል። «አል-ኪታብ» የሚለው የመጽሐፍ ኮርስ እጅግ ይጠቅምሃል። ፍቅር መቼም ሁሌም መንገድ አያጣም።

ሰፊ ራእይ ይኑርህ! ያለ ክርስቶስ በቀር ማንኛውም ሙስሊም የዘላለምን ሕይወት እንደማይወርስ በፍጹም አትርሳ። ይህንን መለወጥ የምትችል ደግሞ አንተ ነህ። ሥራውን ሌላ ሰው እንዲጀምረው አትጠብቅ። ሊተባበሩ ለሚወዱ ሁሉ ግን ፊት አትንሣቸው። አስታውስ! ሙስሊሞችን በወንጌል ለመድረስ በምታደርገው ጥረት ሁሉ ልንረዳህ ሁሌም ዝግጁ ነን።

## ቀጥሎስ?

እጅግ አስቸጋሪ በሆነ ሁኔታ ውስጥ «እንደ እኔ ያለ ሰው የሸሸ . . . ማን ነው?» አለ ነህምያ (ነህምያ 6፡11)። እርግጥ ነው እንደ እርሱ ያለ ሰው አይሸሽም። እንደ አንተስ ያለ ሰው ከእግዚአብሔር ሥራ መሸሽ ይገባዋልን? የለም! አታደርገውም።

ፍጥረት ሁሉ እንዳይጠፋ፥ ወደ ንስሐ እንዲደርስ የእግዚአብሔር ፈቃድ ከሆነ (2ኛ ጴጥሮስ 3፡9)፥ ሁሉም እንዲድኑና እውነትን ወደ መረዳት እንዲደርሱ የሚወድ ከሆነ (1ኛ ጢሞቴዎስ 2፡4)፥ አንተም የእርሱ ምስክር እንድትሆን እግዚአብሔር ይፈልግሃል (የሐዋርያት ሥራ 1፡8)። ሂድና የምሥራቹን ለፍጥረታት ሁሉ አውጅ (ማርቆስ 16፡15)። አሕዛብንም ሁሉ ደቀ መዛሙርት አድርጋቸው (ማቴዎስ 28፡19)። ምን ልታደርግ አሰበሃል?

ከሌሎች ሰዎች ጋር ሲነጻጸር ሙስሊሞች ወንጌልን ለመስማት ያላቸው ዕድል እጅግ አነስተኛ መሆኑን ተገንዘብና አንተም እንደ ኢሳይያስ እንዲህ በል፡-

«ጌታ ሆይ፥ እኔን ላከኝ!» (ኢሳይያስ 6፡8)።

በአገልግሎትህና ለሕይወትህም የሚበጅህን ትምህርት እንደገና ለማገናዘብ የሚረዱህ ጥያቄዎች በሚቀጥሉት ገጾች ላይ ታገኛለህ። ጥያቄዎችን በትክክል መሥራትህን አረጋግጥ። ፍሬ ነገሮቹንም ለጓደኛህ አካፍል፤ ወይም ለእኛም ምን እንደ ተማርክ ጻፍልን። እግዚአብሔር በነገር ሁሉ ይባርክህ። በዙሪያህ ላሉ ሙስሊሞችም በረከት ያድርግህ።

# 12. መግለጫ

## የክለሳ ጥያቄዎች

### ምዕራፍ 1 እና 2

1. እስላማዊው የዘመን አቆጣጠር መቼ ተጀመረ?

   ሀ. በመሐመድ ልደት?

   ለ. መሐመድ ራእይ ማየት በጀመረ ሰሞን?

   ሐ. ወደ መዲና በተሰደደ ጊዜ?

የእስልምናን ባሕርይ ለመረዳት ይህ ክስተት የሚኖረውን ጠቀሜታ ባጭሩ ግለጽ።

2. ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች በአንዳንድ አመለካከቶች ላይ ይግባባሉ፤ በሌሎች ላይ ደግሞ በጣም ይቃረናሉ። ከሁለቱም ነጥቦች ጥቂት ምሳሌዎችን በዝርዝር ግለጽ፤ በምሳሌው መሠረት ምስክርነታችን አስቸጋሪ የሚያደርገውን በተለይ አስረዳ።

3. የአረቢያ አረመኔዎች ከእስልምና በፊት ጣዖታትን ያመልኩ ነበር፤ ጥንቆላንም ይለማመዱ ነበር። በአንተ አመለካከት ይህ ልምምድ እስከ ዛሬ ድረስ በሙስሊሞች ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ ምን ይመስልሃል?

4. «ሰይጣናዊ አንቀጾች» የሚባሉት ምንድናቸው? እስከ አሁንም በቁርዓን ውስጥ ይገኛሉን?

5. መሐመድ ከመጀመሪያ ሚስቱ ከከዲጃ ሞት በኋላ ዓመሉ ከፉኛ ለምን እንደ ተለወጠ የምታውቀውን ሁሉ ግለጽ።

6. ደህሩ-ኡል-ኢስላም እና ደህሩ-ኡል-ሃራብ ምን ማለት ነው? ሙስሊሞች ዛሬ ስለ ተቀደሰው ጦርነት «ጂሐድ» ያላቸው ግንዛቤ ምን እንደ ሆነ ዘርዝረህ አስረዳ።

7. ሙስሊሞችንና እስልምናን ለያይቶ ማየት ለምን ይጠቅማል?

8. የእስልምናን መሠረታዊ እምነቶች ምን ምን እንደ ሆኑ እንደገና ለማጤን ሞክር። እነዚህ አመለካከቶች በሙስሊም ወዳጆችህና ጎረቤቶችህ ሕይወት ውስጥ ምን ምን እንዳስከተሉ፥ ያሳደሩትንም ተጽዕኖ በዝርዝር ግለጽ።

9. የተለያዩ የእስልምና ዓይነቶች ስለ መኖራቸው ምን ታውቃለህ? የየትኛው የእስልምና እምነት ተከታዮች ናቸው በአንተ አካባቢ የሚኖሩት? ስለ እነርሱስ ምን ምን ታውቃለህ? (መልሱን በዚህ መጽሐፍ አታገኝም።)

10. ከመሐመድ ሞት በኋላ እስልምና እንደ ምን ተስፋፋ? ወደ አንተ አገር ወይም ወደ ጎሳህ እንዴት ሊደርስ ቻለ?

## ምዕራፍ 3 ና 4

1. በሚከተሉት ነጥቦች ላይ በመመርኮዝ ስለ ቁርዓንና መጽሐፍ ቅዱስ በማነጻጸር መልስ፡-

| | ቁርዓን | መጽሐፍ ቅዱስ |
|---|---|---|
| ሀ. የመጻሕፍት ብዛት | ______ | ______ |
| ለ. የምዕራፍ ብዛት | ______ | ______ |
| ሐ. የደራሲዎች ብዛት | ______ | ______ |
| መ. የተጻፈበት ዘመን ርዝመት | ______ | ______ |
| ሠ. የአቀማመጥ ቅደም ተከተል | ______ | ______ |

2. የቁርዓን ምንጮች ምንና ምን ናቸው?

3. ሙስሊሞች «የመሻር ደምብ» ብለው ስለ ሰየሙት ነገር አብራ። የቁርዓንን መልእክት ለመረዳት ለምን አስቸጋሪ ሆነ?

4. «ከመሐመድ ጊዜ ጀምሮ ቁርዓን ፈጽሞ አልተለወጠም፤ አልተከለሰም» ብለው ሙስሊሞች ቢከራከሩህ የአንተ ምላሽ ምን ይሆናል?

5. ሙስሊሞች ከቁርዓን በተጨማሪ ሐዲት ለምን አስፈልጋቸው?

6. የሐዲትን ወግ ከአሰባሰቡት መሀል የታወቁት ሁለቱ እነማን ናቸው? የኖሩበትስ ዘመን?

7. የሐዲት ወግ አሰባሳቢዎች ወጎቹን እንዴት ሊመርጧቸው ቻሉ?

8. የሐዲት ይዘት ምንድነው? የሙስሊሙን ሕይወት ምን ያህል ይገዙታል?

## ምዕራፍ 5 ና 6

1. ስለ አምላክ አንድነት የሚያስረዳውን የእስልምና ትምህርት «ታውሂድ» ከመጽሐፍ ቅዱስ አባባል ጋር በማነጻጸር በአጭሩ አስረዳ።

2. የመጽሐፍ ቅዱስ ነቢያትን በሙሉ ሙስሊሞች ያውቁአቸዋል? ያከብሩአቸዋል? የተመለከትሃቸውን ልዩነቶች ግለጽ።

3. በቅድሚያ ስለሚወሰን ዕጣ ፈንታ እስልምና የሚያስተምረው ትምህርት መጽሐፍ ቅዱስ ከሚለው እጅግ ይለያል። አንተስ በግልህ የአገኘኸው አዲስ ግንዛቤ ምንድነው?

4. ስለ ሕይወት መለወጥ እስልምና ምን ያስተምራል? ክርስቲያኖች አንድ ሰው በሕይወቱ ፍጹም ሊለወጥ ይችላል ብለው የሚያምኑት ለምንድነው?

5. ስለ ኃጢአትና ኃጢአቶች ልዩነት አስረዳ። በእግዚአብሔር ፊት ትልቁ ኃጢአት ምንድነው?

6. «ሽርካ» ማለት ምን ማለት ነው?

7. እስልምና «ከሞት በኋላ ሕይወት» ስለሚሆነው ነገር ከሚያስተምረው ትምህርት ምን ልትረዳ ትችላለህ?

8. ወደ ደኅንነት የሚወስደው መንገድ አንድ ብቻ መሆኑን ለሙስሊሞች አጠንክረን ማስረዳቱ ለምን ይጠቅማል?

## ምዕራፍ 7

1. ሙስሊሞች ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ያላቸው ግምት ምንድነው?

2. ሙስሊሞችን ስለ መስበክና ወደ ቤተ ክርስቲያን ስብሰባ ስለ መውሰድ ያለህ ልምምድ ምንድነው?

3. መጽሐፍ ቅዱስ ፍጹም እውነት የተሞላ መሆኑን ለሙስሊሞች የምታስረዳበት መንገድ ምንድነው?

4. ሙስሊሞች መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሥላሴ የሚያስተምረውን ትምህርት እንዴት ይረዱታል?

5. ስለ «ባርናባስ ወንጌል» የምታውቀው ምንድነው?

6. ኢየሱስ ከነቢይ በላይ መሆኑን ለሙስሊሞች የምታስረዳው እንደምን ነው?

7. ኢየሱስ ሊመጣ ያለው መሢሕ መሆኑን ለማሳየት ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በተለይ የምትጠቀማቸው ማጣቀሻዎች የትኞቹ ናቸው?

8. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ «የመስቀሉ እንቅፋት» የሚለው ትርጉም ምንድነው?

9. የክርስቶስን «የማስታረቅ ሥራ» የሚገልጸውን ትምህርት ሙስሊሞች የሚቃወሙት ለምን ለምን ምክንያት ይመስልሃል?

## ምዕራፍ 8

1. አምስት ወይም ከዚያ በላይ መሠረታዊ የወንጌሉን እውነቶች ዘርዝር።

2. «እግዚአብሔር ደኅንነታችን (ኢየሱሳችን) ሆነ» የሚል ዓረፍተ ነገር አንብበሃል፤ ግለጸው።

3. የማቴዎስን ወንጌል ገጽ በገጽ አንብብ። ከዚያም በብሉይ ኪዳን ትንቢቶች መሠረት በትክክል የተፈጸሙትን ክፍሎች ምልክት አድርግባቸው። ቀጥሎም እያንዳንዱን ጥቅስ በንጹህ ወረቀት ላይ ጻፍና በመጽሐፍ ቅዱስህ የውስጠኛው ሽፋን ላይ ለጥፈው፤ ለሌሎችም ለማካፈል ቀላል ይሆንልሃል።

4. ከምታውቃቸው ነገሮች መካከል ሙስሊሞችን በወንጌል ለመድረስ ቅድሚያ የሚሰጧቸው አምስቱ የትኞቹ ናቸው?

5. ክርስቶስን እንደ ግል አዳኛቸው ከመቀበላቸው በፊት ሊያሟሉአቸው የሚገባቸው ቅድመ-ሁኔታዎችን ዘርዝር። ክርስቶስን ሳይቀበሉ በፊት እነዚህን ዘርዝረህ ንገራቸው።

6. ለሙስሊሞች ስለምንሰጠው ምስክርነት 2ኛ ቆሮንቶስ 4፥2 ምን ምን ያስተምረናል?

## ምዕራፍ 9

1. በእግዚአብሔር ኃይል የምንመሰክር ሰዎች መሆን እንዴት ይቻለናል?
2. በወንጌል አገልግሎት ከተሰማራህበት ጊዜ ጀምሮ «ተገዳዳሪ ኃይል» አጋጥሞህ ያውቃልን? ልምምድህን አካፍለን።
3. ወንጌልን በሚገባ ለማድረስ የእኛን ድርሻና የእግዚአብሔርን ድርሻ ለይተህ አስረዳ።
4. ስለ መንፈሳዊ ውጊያ ጠቃሚ የምትላቸውን ነጥቦች ዘርዝር።
5. እውነትና ፍቅርን የሚያዛምዳቸው ምንድነው?

## ምዕራፍ 10 እና 11

1. ለሙስሊሞች የወንጌል አገልጋይ ለመሆን የምትዘጋጅባቸው መንገዶች ምንና ምን ናቸው?
2. «በመሐመድ የማታምነው ለምንድነው?» ሲል አንድ ሙስሊም ቢጠይቅህ የአንተ መልስ ምን ይሆናል?
3. የሙስሊምን ቤት በምትጎበኝበት የመጀመሪያ ጊዜ ቁርዓን ትይዛለህን? ለምን? (ምክንያቶቹን ዘርዝር።)
4. ክርስቲያን መስካሪ ስለ ሃይማኖታዊ ጉዳዮች መከራከር ይገባዋልን? ለምን?
5. አንድ ሰው እንዲህ ብሏል፡- «ሙስሊሞች የሚለወጡት ደረጃ በደረጃ ቀስ በቀስ ነው።» በአባባሉ ትስማማለህን?
6. ከሙስሊም ጋር ውይይት ለመከፈት የሚረዱ ጥቂት ነጥቦችን ዘርዝር።
7. «ስለ እስልምና ምን ታስባለህ?» ለዚህ ጥያቄ መልስ እንዲሆን ለወዳጅህ የምትነግረው ምንድነው?
8. አንድ ሙስሊም ጌታን እንደ ግል አዳኙ እንዲቀበል ከእርሱ ጋር ከጸለይህ በኋላ በደስታ ተውጠሃል። አዲሱን አማኝ የምትረዳባቸው ተከታይ እርምጃዎች ምንና ምን ይሆናሉ?

9. የ«ሐራም» ና የ«የሐላል»ን ትርጉም አስረዳ። እነዚህ ነገሮች ከክርስቲያኖች ይልቅ የሙስሊሞችን ትኩረት እንዴት ሊስቡ ቻሉ?

10. ይህን ዓረፍተ ነገር አሟልተህ ጻፍ፤ ሙስሊሞችን በወንጌል ለመድረስ የምዕመናን ሁሉ . . .

11. በክርስቶስ ወንጌል ሙስሊሞችን ለመድረስ ከምንጠቀምባቸው ዓይነተኛ ዘዴዎች ጥቂቶቹን ግለጽ።

«የሕይወት በር» የሕትመት ውጤቶች፡-

| የክርስቲያን ስንቅና ትጥቅ |

## ስለ እነዚህስ አይገድህምን?

* በገርሃርድ ኔልስ በ1992 እ.ኤ.አ. የተዘጋጀ አነስተኛ መጽሐፍ

* ወንጌልን ለሙስሊሞች ለማሰራጨት ሊያጋጥም የሚችለውን ፍጥጫ እና ለእኛም የተከፈተውን የወንጌል በር እንድናይ ዓይን ከፋች መረጃ የሚሰጥ ዝግጅት

* ከሰሐራ ደቡብ ባሉ የአፍሪካ አገሮች ውስጥ በአንድነት የሚኖሩትን ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች ልዩ ሁኔታ ግምት ውስጥ በማግባት ክርስቲያኖች ይህንን ዕድል ለወንጌል ስርጭት ለምን እንዳልተጠቀሙበት ስድስት ምክንያቶችን ይጠቁማል።

* ደራሲው ለብዙ ዓመታት ያህል ለሙስሊሞች ሲመሰክር የአካበተውን ልምድ በመንተራስ አንባቢው ተበራቶ ሌሎችንም ክርስቲያኖች አስተባብሮ ሙስሊሞችን በወንጌል ለመድረስ ስልት እንዲነድፍ የሚረዳው ተግባራዊ ምክሩን የአካፈለበት መጽሐፍ ነው።

* መጽሐፉ በሥዕሎች፥ በመጠይቆች፥ የተግባራዊ እቅድ ቅጽ የተጠናከረና ለቁም ነገረኛ አንባቢ ደግሞ የሚውል የክለሳ ጥያቄዎችን፥ እንዲሁም ተሞልቶ የሚላክ የውሳኔ መግለጫ ቅጽ አብሮ ይዟል።

* መጋቢዎችና የክርስቲያን ኅብረቶች መሪዎች የግድ ያስፈልጋቸዋል።

## ለሙስሊሞች ጥያቄዎች የክርስቲያኖች መልሶች

* በገርሃርድ ኔልስ በ1980 እ.ኤ.አ. የተዘጋጀ
* እስልምና ስለ መጽሐፍ ቅዱስ፥ ስለ ጌታ ኢየሱስ መለኮታዊነት፥ ስለ እግዚአሔር ወልድነቱ፥ ስለ መስቀል ላይ ሞቱ፥ ስለ እርቅ፥ ስለ ሥላሴ፥ ወዘተ የሚያናፍሰውን ሐሰተኛ ትምህርት መልስ እንዲሆን ከቅዱሳት መጻሕፍት፥ ከታሪክና ከሐቅ የተቀናበረ ምላሽ የያዘ መጽሐፍ
* በአሁኑ ጊዜ ሙስሊሞች ክርስትናን ለመውጋት የሚጠቀሙበት ስለ ሐሰተኛው «የባርናባስ ወንጌል» ምንነት የሚያስረዳ ልዩ ምዕራፍ ያለው መጽሐፍ
* መጽሐፉ ለክርስቲያኖች በይበልጥ ጠቃሚ ቢሆንም አመዛዛኝ ሕሊና ያለው ሙስሊምም እምነቱን ዘወር ብሎ እንዲፈትሽ በክርስቶስና በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ያለውን አመለካከት እንዲመዝን ያደርገዋል።

## የመምህሩ መርጃ

* በ1992 እ.ኤ.አ. በገርሃርድ ኔልስ የተዘጋጀ መጽሐፍ
* ለሙስሊሞች ወንጌልን ለመስበክ ተግባራዊና ስልታዊ አቀራረብ

  እንድረስላቸው (የተማሪው መርጃ መጽሐፍ)
* በገርሃርድ ኔልስ የተዘጋጀ (1992)
* ከላይኛው ዝግጅት ጋር አብሮ የሚሄድ
* በቀላል የቋንቋ አቀራረብ፥ ከማጠናከሪያ ታሪኮች ጋር የተዘጋጀ

* ለማንኛውም ክርስቲያን የሚሆን ቀላል አቀራረብ ያለውና ለሙስሊሞች ወንጌልን ማድረስ የሚቻልበትን ዘዴ የሚያስተምር

**በተለይ ለሙስሊሞች የተዘጋጁ**

## እቅድና ግብ

* በ1986 እ.ኤ.አ. በገርሃርድ ኔልስ የተዘጋጀ
* የወንጌልን ይዘትና አመጣጥ ያሳያል።
* ብዙ ማጣቀሻዎችን ከቅዱሳት መጻሕፍት ይዟል፤ ቁርዓንን ግን አይጨምርም።
* ጥሩ ማስጀመሪያ ነው።

## ላለመደናገር ማወዳደር

* በገርሃርድ ኔልስ እ.ኤ.አ. 1986 የተዘጋጀ
* ሙስሊም አንባቢ የማያውቀውን ሌላ ታሪክ ከክርስቲያኖች እንዲሰማ እንዲረዳ የሚጋብዝ የሚያግባባም ጽሑፍ
* የመጽሐፍ ሁለት ክፍሎች ቁርአን ስለ መጽሐፍ ቅዱስና ስለ ጌታ ኢየሱስ የሚመክረውን ምስክርነት ይተነትናሉ።
* ቀጥሎም ደግሞ ስለ ትንቢቶችና አፈጻጸማቸው የመጽሐፍ ቅዱስን መረጃዎች ያቀርባል።
* በመጨረሻም አንባቢው የደረሰበትን ድምዳሚ ያለ ሌሎች ተጽዕኖ በራሱ ውሳኔ ብቻ እንዲገልጽ ይጠይቃል።
* እውነትን እየፈለገ ላለ አሰላሳይ እጅግ ጠቃሚ ዝግጅት ነው።

## የውኃ ላይ ኩበት

* ገርሃርድ ኔልስ በ1986 የአዘጋጀው አነስተኛ መጽሐፍ

* ቀድሞውኑ ስለ ተወሰነ ዕጣ ፈንታና (ፕሪዴስቲኔሽን) ስለ ነጻ ፈቃድ በቁርዓንና በሐዲት ውስጥ የሰፈረውን የተምታታ አሳብ በመሳል አንባቢው ከእውነቱ ጋር እንዲጋፈጥ ያደርገዋል።

* ስለ ኃጢአት ይቅርታ፥ ስለ ፍቅርና ስለ ደኅንነት ምሳሌ የሚሆነን ሳሙኤል ስለሚባል ሰው ታሪክ ያስነብበናል።

* የሚዘገንኑ የቁርዓን ጥቅሶችን በማየት ሙስሊሙ አንባቢ ራሱን እንዲመረምር ያደርጉታል።

* ምናልባትም ሙስሊም ለመሆን የሚያስቡት ክርስቲያኖች ካሉ ጥሩ የመመለሻ መልእክትነት አለው።

## ውድ ዐብደላ

* በገርሃርድ ኔልስ በ 1986 እ.ኤ.አ. የተዘጋጀው

* በደብዳቤ መልክ የተቀናበሩ 10 መልእክቶች ናቸው፤ በሙስሊሞችና በክርስቲያኖች መካከል መረዳትና መግባባት እንዲፈጠር ያዘጋጃል።

* ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ዋና ዋና ጉዳዮች ይዟል፡-

1. የእግዚአብሔር እውነት በሕይወታችን መገለጥ አለበት
2. «መጽሐፍ ቅዱስ ተበርዟል» የሚባለው ከሐሜታ አያልፍም
3. በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ያሉት ትንቢቶችና ፍጻሜአቸው በእርግጥ ልዩና ዓይነተኛ ማስረጃዎች ናቸው
4. ቁርዓን የአምላክን ማንተም ይዟልን?
5. የባርናባስ ወንጌልና ኋላ የመጣ «ስርዝ-ድልዝ»
6. የኃጢአትና ኃጢአተኝነት ትርጉም
7. የእግዚአብሔር ስጦታ የሆነው ጽድቅ
8. ከነቢይም የሚበልጠው - ኢየሱስ
9. የሞትና የሕይወት ምርጫ - በመስቀሉ ላይ
10. መለወጥ፡- ከመመለስም ይበልጣል

* ተራው ሙስሊም ሁሉ የሚወዳቸው ደብዳቤዎች ናቸው።

* በጽሑፉ ውስጥ ጸሐፊው ለሙስሊሞችና ለእግዚአብሔር ያለውን ፍቅር በእርግጥ ያዩበታል።

## የነቢ ዒሳ መልእክት

* በገርሃርድ ኔልስ የተዘጋጀ (1992)

* ሙስሊሞች ኢየሱስ ነቢይ ወይም መልእክተኛ ብቻ ነው የሚለውን ትምህርታቸውን ይመረምራል።

* «መልእክተኛ ከሆነ ይዞት የመጣው መልእክት ምንድነው?»

* ኢየሱስ ስለ ራሱና ስለ መልእክቱ የተናገረውን በዝርዝር የሚያስረዳ መጽሐፍ ነው።

* በመጽሐፉ ማጠቃለያም ሙስሊሙ ስለ አለበት የሕይወት አጣብቂኝ በእውነት የታወቀ መሆኑን ገልጾ የተረጋገጠውን የሕይወት ጎዳና እንዲከተል ይጋብዛል።

* ብዙ ሙስሊሞች በጉጉት ያነቡት ይሆናል።

## ስለ መሢሑ ልንገራችሁ?

* በሲ. አር. ማርሽ የተዘጋጀ በራሪ ጽሑፍ (1988)

* እጅግ በተጠቃለለ ሁኔታ የመሢሑ ኢየሱስን «ልዩ ስብዕና» መለኮታዊነትም ያስረዳል። ትራክቱ በጥያቄ መልክ የተዘጋጁ አሥር ክፍሎች አሉት፡-

- ስለ አስደናቂ ውልደቱ ምን ታስባለህ?

- ስለ ባሕርያቱ ምን ታስባለህ?

- ስለ ንግግሩ ምን ታስባለህ?

- ስለ ስሙና መጠሪያዎቹ (ማዕረጉ) ምን ታስባለህ?

- ስለ ኃይሉና ሥልጣኑ ምን ታስባለህ?

- ስለ ሥቃዩ ምን ታስባለህ?

- ሞትን ድል ስለማድረጉ ምን ታስባለህ?

- ስለ ዕርገቱ ምን ታስባለህ?

- ስለ ዳግም ምጽዓቱ ምን ታስባለህ?

- ከአንተስ ምን እንደሚፈልግ ታስባለህ?

* የዝግጅቱ መግቢያ አል-መሲሕ ምን ማለት እንደሆነ ማብራራት ይጀምራል።

* አስገራሚ የማጠናከሪያ ታሪኮችና ትምህርቶችንም ይዟል።

* ትራክቱ ለሙስሊሞች በቤተ ክርስቲያን አማካይነት የሚታደል ነው።

## አል - ኪታብ

## ለሙስሊሞች የተዘጋጀ የመጻጻፍ ትምህርት

* በ1985 ዓ.ም. በገርሃርድ ኔልስ የተዘጋጀ መጽሐፍ

* 18 ትምህርቶች አሉት። ስለ መጽሐፍ ቅዱስ፥ ሰው፥ ኃጢአት፥ የእግዚአብሔር ሕግ፥ ስለ ኢየሱስ ሕይወት፥ መንፈስ ቅዱስ፥ በእግዚአብሔር ሰላም ስለ ተሞላ አስገራሚ ሕይወት . . . እነዚህን ነጥቦች ሁሉ የሚዳስስ ይዘት አለው።

* የመጽሐፍ ቅዱስ አመለካከት የቀረበው ሙስሊሞች ከእስልምና የማያገኙትን መልስ በሚያግዝ ሁኔታ ነው። ስለ ዋስትና፥ የኃጢአት ይቅርታ፥ ደኅንነትን በሚገባ ያስረዳል።

* ተማሪው ጥናቶቹን ለማጥናት በእርግጥ መጽሐፍ ቅዱስ መያዝ አለበት። ሲያጠቃልልም ኮርሱን በተመለከተ ፈተና ይቀርብለታል።

* መጽሐፉን በደንብ ለማጥናትና በቂ ግንዛቤን እንዲያገኝ ሙስሊሙ ተማሪ በሌሎች ክርሲትያኖች ቢረዳ መልካም ነው (የሐዋርያት ሥራ 8፡35)።

የሁሉም መጻሕፍት ዝርዝርና ዋጋ ብትጠይቀን እንልክልሃለን።

# ለሙስሊሞች ወንጌልን ለመመስከር የሚረዱ ጠቃሚ መግለጫዎች

መግለጫዎች፥ ታሪኮች፥ ምሳሌያዊ ትምህርቶች ወጣት ቢሆን ሽማግሌ፥ ሀብታም ወይም ድሀ፥ ምሁር ወይም መሐይም፥ የሁሉን ሰው አሳብ ለመጨምደድ፥ ትኩረታቸውንም ለመሳብ እጅግ ይጠቅማሉ። የአድማጩን ስሜት እያዝናኑ እንግድነት ሳይሰማው ተፈላጊውን ነጥብ በኃይልና በማይረሳ መንገድ እንዲያደምጥ ያደርጉታል። ጌታ ኢየሱስ ለወዳጆቹ ቢሆን ለተቃዋሚዎቹ እንደየሁኔታቸው ለማስተማር፥ ሲከራከሩትም ለመመለስ ታሪኮችንና መግለጫዎችን በመጠቀም ትምህርቱን ያስረዳ ነበር። እስቲ አንተም ሞክረው።

የማጠናከሪያ አሳቦች ከብዙ አቅጣጫ ሊሰበሰቡ ይችላሉ፤ ከታሪክ ማኅደር፥ ተረታ ተረቶች፥ ልብ ወለዶች፥ ግላዊ ልምምዶች፥ ድራማዎች፥ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮች፥ የታላላቅ ሰዎች አባባሎች፥ ታሪክና ምሳሌዎች፥ ገጠመኞች፥ እነዚህ ሁሉ የማጠናከሪያ አሳብ ለማቀናጀት ይጠቅማሉ።

ቀጥሎ ያሉት ምሳሌዎች የበለጠ ያስረዱሃል፡-

## ሳሙኤል የኮክሰስ አገር ልዑል

(ከታሪክ ማኅደር)

ሳሙኤል ከ200 ዓመታት በፊት የኖረ የኮክሰስ አገር ልዑል ነበር። በዘመኑም ሕዝቡ ከቱርኮች ጋር የማያቋርጥ ውጊያ ውስጥ ነበር። ከዕለታት አንድ ቀን ሠራዊቱን እየመራ አንዲት የቱርክ ከተማ ሊያጠቃ ከበበ። ሁልጊዜ እንደምታደርገውም እናቱ ከእርሱ ጋር ዘምታ ነበር። በዚያው ሰሞን አንድ ሌሊት ድንገተኛ ጥቃት ሰንዝሮ ከተማይቱን ለመማረክ ዕቅድ አወጣ፤ ጦሩም ተንቀሳቀሰ። ነገር ግን ምሥጢራዊው ዕቅድ ሾልኮ ነበርና ጠላት መንገድ ደፍጦ ጥቃቱን መለሰ። ዕቅዱም ከሸፈ።

የሳሙኤል ቁጣ ነደደ። ይህ ወሬ አቀባይ ከተገኘ አንድ መቶ ጅራፍ እንደሚቀጣ አዋጅ አወጣ። ከፊተኛው ይልቅ እጅግ ምሥጢራዊ የሆነ ሌላ የጦር ዕቅድ አወጣና እንደገና ለድንገተኛ ጥቃት ዘመተ፤ ዳሩ ግን አሁንም ድል ከእርሱ ራቀ፤ አልሆነለትም።

በዚህ ጊዜ ግን ወሬ አቀባዩ ታወቀ፤ የሳሙኤል የራሱ እናት ነበረች። ሳሙኤልም ለሦስት ቀናት ከድንኳኑ ሳይወጣ ለሕዝብም ሳይታይ ከረመ። ምን ቢያደርግ እንደሚሻለው ሲያወጣና ሲያወርድ አሳለፈ። ከቅጣቱ እናቱን ቢያድናት፥ ሠራዊቱ ሁሉ «ፍርደ ገምድል» ሊለው ነው፤ ቢቀጣትም «ይህስ እንዴት ያለው ነው? ለእናቱ እንኳን የማይራራ?» ሊሉት ነው፤ ምን ያድርግ?

ቆይታው ልባቸውን ያንጠለጠለው ሕዝቡ ሠራዊቱም ተሰልፎ ሲጠባበቀው፥ ባለበት በሦስተኛው ቀን ሳሙኤል ከድንኳኑ ብቅ አለ። እልኹ ገና እንዳልበረደለት ያስታውቃል። አለም፤ «ወሬኛ በመካከላችን ሰርጎ ገብቶ ኖሮ ሁለት ድሎች አምልጠውናል። ሰዎቻችንም ተገድለውብናል፤ እንግዲህ ይቅርታ ብሎ ነገር የለም፤ ወንጀል ተፈጽሟል፤ በሕጌ መሠረት ወንጀለኛው መቀጣት አለበት፤ አሁኑኑ መቶ ጅራፍ። ጽድቅና ፍትሕ የሚከበረው እንዲህ ነው» አለ።

ወሬ አቀባይዋ እናቱም እየተንቀጠቀጠች ወደ መገረፊያው ቦታ ተወሰደች፤ ፊቷ ጭው! ብሎ ወዘናዋ ሁሉ ሸሽቷት በመገረፊያው መድረክ ላይ ወጣች። ገራፊው ከንዱን መዘዘና ጅራፉን አነሣ . . . አቤት! አወናጭፎ ከማሳረፉ በፊት ሳሙኤል «ቆይ» አለ በጩኸት፤ «ቆይ! እርሷ እኮ እናቴ ናት። ከሥጋዋ ሥጋ የነሣሁ ከደምዋም የተቀዳሁ ልጇ ነኝ። ስለዚህ ቅጣቱን ስለ እርሷ እኔ እቀበላለሁ» አለ።

ሳሙኤል ልብሱን አወለቀና በመገረፊያው መድረክ ላይ ወጣ። «ስማ! ገራፊ . . .» አለ፤ «አንተ ወንጀለኛ ገራፊ ነህና፤ እኔን ከማንኛውም ወንጀለኛ ባነሰ ሁኔታ ለመገረፍ እንዳታስብ! በል ቀጥል!» አለ።

ከዚያም ግርፋቱ ቀጠለ፤ ጅራፍ በጅራፍ ላይ ተደራረበ፤ ሳሙኤል ሕሊናውን ሳተ፤ ወደቀም። ይሞታል ተብሎ ሲጠበቅ እንደማይተርፍ የለም ተረፈ።

ይህ ታሪክ ከማንኛውም ታሪክ በላይ የክርስቶስን አርአያነት የሚገልጽ ነው። እርሱ የሰውን ሥጋ የለበሰ አምላክ ነበር። ጽድቅንና ፍትሕን ማድረግ ግዴታው ነው፤ ነገር ግን ከኃጢአታችን የተነሣ ሊደርስ ያለብንን ፍርድ ስለ እኛ በመስቀል ተሰቅሎ ከፈለልን።

## ዕንቁ አውጪው!

(እውነተኛ ታሪክ)

በሕንድ ምሥራቃዊ የባሕር ዳርቻ የኖረው ሽማግሌው ዕንቁ አውጪ ለሚቀጥለው ሕይወት ለመዘጋጀት በማሰብ ቀሪ ዘመኑን ለሃይማኖታዊ ጉዳዮች ሰጥቶ ለመኖር ወሰነ። አእምሮውም በ«ቅዱስ» ጊንጀስ ወንዝ ዳርቻ ወደምትገኘው ቤናሬስ ወደ ተባለች «ቅድስት» ከተማ በጉልበቱ ተጉዞ እንዲሄድ ገፋፋው። ይህም ሰው ክርስቲያን ጓደኛ ነበረውና የመሰናበቻ ግብዣ አድርጎለት ስለ ጉዞው ያጫውተዋል። የዕንቁ አውጪው ብቸኛ ወዳጅ ይህ ክርስቲያን ብቻ ነበርና ከእርሱም ሌላ በዕለቱ ማንም አልነበረም።

ምግብ ከበሉ በኋላ ዕንቁ አውጪው ስለ ተቀደሰ ጉዞው ያለውን እቅድ በዝርዝር አቀረበ። ወዳጁ ግን ሀሳቡን እንዲለውጥ ብዙ መከረው፤ ጉልበቶቹ ተላልጠው እንደሚቆስሉና በሳቢያውም እንደሚሞት ነገረው። ዕንቁ አውጪውም መልሶ እንዲህ አለ፤ «ወደ ቅዱስ ጊንጀስ ወንዝ ስጓዝ ብሞት፥ ነፍሴ እንደምትሸለም አምናለሁ» አለ።

ጥቂት ቆይቶም በዚያው ምሽት ከጓደኛው ጋር ተሰነባብተው ከመለየቱ በፊት፥ የዕንቁ አውጪው ሣጥኑን ፈቀቅ አድርጎ ዕቃ የሚደብቅበት ቦታ ታየ። ኩራዙን በሚያበራው አነስተኛ ብርሃን ከዚያ ውስጥ የተለየ ውበትና ቅርጽ ያለውን ትልቅ ዕንቁ አወጣ። «አንተ ለእኔ ብቸኛ ወዳጄ ነህ፤ ከአንተም ሌላ ጓደኛ እንደ ሌለኝ ታውቃለህ፤ ስለዚህ ይህችን ዕንቁ ልሰጥህ እፈልጋለሁ» አለው።

«ይህ የከበረ ነገር ነው» አለ ጓደኛው፤ እርሱም «እኔ እንዲህ ያለ ስጦታ መቀበል አልችልም» አለው። የዕንቁ አውጪውም በዓይነ ሕሊናው ወደ ኋላ ተጉዞ የአሳለፈውን ዘመን ከፈተሸ በኋላ መናገር ጀመረ፤ «እኔ አንድ ወንድ ልጅ ነበረኝ። በዚህ የባሕር ዳርቻ እንደ

እርሱ ያለ ዋናተኛ ዕንቁ አውጪ አልነበረም። ከእኛ ከሁላችን በላይ ጠልቆ መዋኘትና እዚያ በጥልቁ ረዥም ጊዜ ሊቆይ ይችል ነበር። አንድ ቀን እንደተለመደው ዕንቁ ለመሰብሰብ በውቃው ዳርቻ ላይ ጀልባችንን እየቀዘፍን ሳለ ልጄ ከጀልባዋ ላይ ወረደና እየዋኘ ወደ ጥልቁ ወረደ። እንዲህ ማድረጉ ዛጎሎችን ሰብስቦ ለእኔ እንዲሰጠኝና እኔም ተቀብዬ በሰንጢ ለመክፈት እንድችል ነው።

«ከዚያም እንዲህ ሆነ፤ በጣም ትልቅ ዛጎል ከውቃው ታችኛው ወለል ላይ ተመለከተ። እርሱንም ለማምጣት ወረደ። ዛጎሉ ግን ከሌላ ነገር ጋር የተጣበቀ ነበርና አልቻለም። ለማላቀቅ ታገለ፤ አልሆነለትም። ጊዜው እየጨመረ ቢሄድም ተስፋ ሳይቆርጥ ሞከረ። ከብዙ ትግል በኋላ ግን ተስፋ ባለመቁረጡ ይዞት ወጣ። ወዲያው ግን ደም ከአፋ ፈለቀ። ወደ ታንኳይቱ ሳስገባው እጄ ላይ ሕይወቱ አለፈች።

«በኋላም ዛጎሉን ስከፍተው ይህን ዕንቁ አገኘሁ። ለእኔ ከዚህ የበለጠ ውድና የተከበረ ነገር የለምና ልሸጠው አልቻልሁም» አለ።

«ይህ የከበረ ነገር ነው፤ ዋጋውን እንኳ በሙሉ ልከፍል ባልችል ጥቂት ነገር እንድከፍልህ ፍቀድልኝ፤ ለምሳሌ አንድ መቶ ፓውንድ!» ብሎ ለመነው ጓደኛው።

ዕንቁ አውጪውም በመልሱ ስሜቱ ተነክቶ «ልጄ ለሞተበት ነገር መቶ ፓውንድ ልትከፍለኝ ትፈልጋለህን? የልጄን ዋጋ ማንም ችሎ ሊከፍለኝ አይችልም፤ ነገር ግን በነጻ እንድትወስደው ልሰጥህ እፈልግ ነበር» አለው።

ክርስቲያን ጓደኛውም ተነሥቶ አቀፈውና «ሰማህ ወዳጄ! ላሳዝንህ ብዬ እንኳ አይደለም። አንተ ግን እግዚአብሔር በልጁ ሞት የከፈለውን የኃጢአት ዕዳ በጉልበትህ ለመክፈል ጥረት እያደረግህ መሆኑ ይታወቅሃልን? በገንዘብ ሊተመን የማይችል ስጦታ የሰጠህ እግዚአብሔርን ስጦታውን ‹አልቀበልም› ብትለው እንዴት እንደምታሳዝነው አስበኸው ይሆንን?» ሲል መለሰለት።

---

ዕንቁ አውጪው ምሥጢሩ ወዲያው ተገለጠለት። በጉልበቱ እየዳኸ ወደ ቤናሬስ ወንዝ ሊያደርግ የነበረውን ጉዞ ሰረዘ። የእግዚአብሔር

---

ስጦታ የሆነውን ጌታ ኢየሱስን ግን ባለበት በጸሎት ተንበርክኮ ተቀበለ። የኃጢአት ይቅርታንም ተጎናጸፈ።

## የውለታው ምላሽ

(ገጠመኝ)

እንግዳን ማስተናገድ የሙስሊሞች ዓይነተኛ ባሕርይ ነው። ወደ ሙስሊም ቤት ጎራ ባልህ ቁጥር ሌላው ቢቀር ሻይ ደጋግመህ ትጋበዛለህ። የብዙ ጊዜ ሙስሊም ወዳጁን ሊጎበኝ የሄደ አንድ ክርስቲያን ከሻይ ግብዣ በኋላ ኪሱን ዳበስ አደረገና የገንዘብ ቦርሳውን አወጣ፤ ከዚያም አለ፤ «እስከ አሁን በቤታችሁ ውስጥ ስለ አደረጋችሁልኝ ግብዣ በጣም አመሰግናለሁ። የዛሬዋን ግብዣ ግን ብከፍላችሁ ደስ ይለኛል» አለ። ሙስሊሙም ባነጋገሩ እንደ መደናገር ብሎ የሚመልሰውን ቃል እየመረጠ «በጭራሽ ልትከፍል አትችልም!» አለ። ክርስቲያኑ ግን ሳንቲሙን በጣቶቹ እንደ ያዘ መክፈል እንዳለበት አጥብቆ ተናገረ። በዚህን ጊዜ የሙስሊሙ ፊት ደም መሰለ። በቁጣም ተናገረ እንዲህ ሲል:- «እንግዳን ለማስተናገድ ስለምንወድ ነው ሻዩን የሰጠንህ። ለጋበዝንህ ሻይ ገንዘብ መቀበል ለእኛ ስድብ ነው» አለ።

ሙስሊሙ ይህን እየተናገር ሳለ፥ የአስተናጋጁ ልጅ በአጠገቡ ሲያልፍ አየና ሳንቲሙን ሰጠው። አመስግኖ ተቀብሎ ሄደ።

ከዚህ ምን እንማራለን? የሰውየውን ነገር እንተውና እኛስ በሰማያዊ በረከት ሁሉ የባረከን አምላካችንን ስለ አደረገልን ሁሉ የምንሰጠው ምላሽ ምንድነው?

## የወንበር ምሳሌ

(በዕቃ ተጠቅሞ ማስተማር)

ይኼኛው ታሪክ ስለ እውነተኛ እምነት ያስተምረናል። እውነተኛ እምነት በአእምሮ አይመዘንም፤ ለምታምነው እውነት ራስህን አሳልፈህ መስጠት ነው እንጂ።

የሙስሊም ቤት ስትጎበኝ፥ አስቀድሞ መቀመጫ ተሰጥቶህ ከሆነ በውይይትህ በሚመችህ ጊዜ ተነሣና ወንበሩን በእጅህ ይዘህ በመቆም ገለጻህን ቀጥል በምሳሌ፡-

«ወደ እናንተ ዘንድ በመጣሁ ጊዜ በአክብሮት ተቀበላችሁኝ፤ የምቀመጥበትንም ወንበር ሰጣችሁኝ። ስለዚህም ላመሰግናችሁ እወዳለሁ። ነገር ግን አሁንም እንዲሁ እንደ ቆምሁ የምነግራችሁ ነገር አለኝ። ምናልባት እንደገና እንድቀመጥ ትጋብዙኝ ወይንም ባለመቀመጤ ትደነቁ ወይንም ደግሞ ለመቀመጥ የፈራሁ ይመስላችሁ ይሆናል። በእርግጥ ወንበሩ እንዳይጥለኝ ልሠጋ እችላለሁ። አንዳንድ ወንበሮች ጥንካሬ ስለ ሌላቸው ሲቀመጡባቸው እየተሰበሩ ሰዎችን እንደሚጎዱ አውቃለሁ። እኔ ግን ይህንን ወንበሩ ላይ በጥንቃቄ በመቀመጥ (እየተቀመጥሁ) ክብደቴን ለመሸከም የሚችልና የማይችል መሆኑን ራሴው አረጋግጣለሁ። ለምሳሌ አሁን ይህን ወንበር አምኜዋለሁ፤ ጥንካሬውን ስለ ተማመንሁበትም ይኼው! ራሴን ጥዬበታለሁ።

«የወንበሩ ጥንካሬ የታወቀው ስቀመጥበት እንደ ሆነ ሁሉ በእግዚአብሔር ላይ ያለን እምነት ደግሞ የሚረጋገጠው የእግዚአብሔር ስጦታ በሆነው በመሢሑ እና በአዳኙ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ላይ እምነታችንን ስንጥል ነው። እርግጠኛ ሆኜ እነግራችኋለሁ፤ እምነታችንን ብንጥልበት እርሱ ሊሸከመን ሙሉ ኃይል ያለው ነው።»

## ከእስር ለመፈታት

(የግል ልምምድ)

ከጥቂት ዓመታት በፊት ባለቤቴ ተከሳ ፍርድ ቤት ቀርባ ነበር። የተከሰሰችበት ምክንያት የትራፊክ ሕግ ስለ ጣሰች ነበር። ቅጣትም እንዳይከብድባት በዕለቱ የነበረባትን አስቸኳይ ጉዳይ ለዳኛው ነግራ ከተወሰነው በላይ በፍጥነት በማሽከርከሯ ይቅርታ እንዲደረግላት ጠየቀች። አልሆነላትም። አምሳ ዶላር ተቀጣች። ምሕረት እንደማይደረግላት ስታውቅ ከቦርሳዋ ውስጥ ቼክ አውጥታ ለገንዘብ ያዢው ስትሰጥ በጥሬ ገንዘብ ካልሆነ በስተቀር እንደማይቀበላት ገለጸላት።

«እሺ ወደ ባንክ እንሂድና ገንዘቡን አውጥቼ ልስጣችሁ» አለች።

«አትችይም፤ ሳትከፍይ ከዚህ ሕንጻ መውጣት አይፈቀድም።»

«እሺ ምን ላድርግ?»

«አንድ የስልክ ጥሪ እንፈቅድልሻለን፤ ስልክ ደውለሽ ገንዘቡን ሰው እንዲያመጣልሽ ማድረግ ትችያለሽ፤ አለዚያ 5 ቀን ታሥረሽ ትቆያለሽ» አላት። ከዚህም በኋላ ባለቤቱ በኃዘን ተሞልታ ስልክ ደወለችልኝ። ወደ ፍርድ ቤት ሄጄ ቅጣቱን ከፈልሁ፤ አስፈታኋትም። ይህንን አጋጣሚ ሚስቴ ሁል ጊዜም ታስታውሰዋለች።

> ከዚህስ ምን እንማራለን? ሰው እግዚአብሔር የፈለገበትን ሁሉ ለመፈጸምና ደግ ሥራ እየሠራ ለመኖር ቢጥር አይሆንለትም። የእግዚአብሔርን ቅዱስ ሕግ ከአፈረስን በኋላ እኛ በመሰለን መንገድ ሳይሆን እግዚአብሔር በቅዱስ ቃሉ በወሰነው መንገድ ብቻ ይቅርታ እናገኛለን። «መዳን በሌላ በማንም የለም፤ እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና» (የሐዋርያት ሥራ 4፡2)።

## መልካም ወይስ ክፉ ወሬ

ከቤት ወደ ቤት እየተዘዋወርን ሙስሊሞችን ስንጎበኝ ሰዎች ዜና ሲያደምጡ ወይንም በቴሌቪዥን ሲመለከቱ ሊያጋጥመን ይችላል። ታዲያ ሰው ቤት ገብተን ሬድዮና ቴሌቪዥን ከመዝጋት ይልቅ፣ ምስክርነታችን እንዳይሳካ እንቅፋት እንዳይሆንብን የሰዎቹን ትኩረት ማዞር ይገባናል።

«ስላቋረጥኳችሁ ይቅርታ! የዛሬው ዜና አስደሳች ነገር ይበዛዋል ወይስ የሚያሳዝኑ እኔ እንደሚመስለኝ መጥፎው ወሬ ይበዛል፤ አይደለም እንዴ? ለምን ይመስላችኋል?» መልስ ከሰጡ በኋላ እንደገና ልንቀጥል እንችላለን፤ «ጥቂት ደቂቃዎች ወስደን ይህን ጉዳይ እንድንመለከት አንዳንድ ጥያቄዎች እያነሣን ብንወያይ እናስቸግራችሁ ይሆን?» በገፅ 127 ያሉትን ጥያቄዎች ይመልከቱ።

## የነጻነቱ በር

(ልብ ወለድ)

በባዕድ ምድር የሚኖሩ የአንድ ንጉሥ ወዳጆች የነበሩ ሦስት ሰዎች ችግር አጋጠማቸውና ወህኒ ታሰሩ። ንጉሡም ሲሰማ እጅግ አዘነና እንዲያስፈታቸው ልጁን ወደ እነርሱ ላከው። ልጁም የወህኒውን ዘበኛ በኃይል አንበረከከና የወህኒውን ቁልፍ መክፈቻ ወስዶ ከፍተው እንዲወጡ በመስኮቱ ቀዳዳ በኩል ለእስረኞቹ አቀበላቸው።

ዳሩ ግን የተሰጣቸውን እድል በቶሎ በመጠቀም ፈንታ እስር ቤቱ ወለል ላይ ተቀመጡ፤ ቁልፉንም እያገላበጡ እያዩ መመርመር ጀመሩ። እስር ቤቱን እንደሚከፍት ፈጽሞ ስለ ተጠራጠሩ፥ ስለ ቁልፉም የየራሳቸው አስተያየት እየሰጡ መወያየት ቀጠሉ። ይባስ ብለውም የመክፈቻውን ቅርጽ ለመለወጥ በሚመስላቸውም መንገድ አቃንተው ለመጠቀም በመቀጥቀጥ ቁልፉን ቸረቸፉት። በመጨረሻም ለመውጣት ተዘጋጁና መክፈቻውን ሲሞክሩ ሊከፍትላቸው አልቻለም። ጭንቀት ብቻ። በንጉሡም ልጅ አፌዙበት፤ ቀድሞውኑ የሚሠራ ቁልፍ መች አመጣህና በማለት። እስራታቸውም እንደ ጸና ቀረ።

| |
|---|
| ከዚህ ታሪክ ደግሞ ወንጌሉን ሰምተው ቀና ምላሻቸውን ከመስጠት ይልቅ የሚያጣምሙትን፥ የሚቀንሱትን፥ የሚጨምሩትን፥ በመጨረሻም ፈጽሞ ላለመቀበል የሚቃወሙትን የአሳዛኝ ሰዎች ፍጻሜ እናስታውሳለን። |

## ገበሬውና ድመቲቷ

(ተረት)

ለእንስሳት ትልቅ ፍቅር የነበረው አንድ ቃዲ (የሙስሊም ሹመኛ) ነበር። ከቤት እንስሳዎቹ የበለጠ የሚከራባትና የሚወዳት አንታር የተባለች ድመት ነበረችው። አንታር ለቃዲውና ለእንግዶቹ ሻይ እያፈላች የምታስተናግድ ሥልጡን ድመት ነበረች።

አንድ ቀን አንድ ገበሬ ወደ ቃዲው ቤት ሄደና በኑሮው ላይ ስለ አጋጠመው ችግር ስለ ወለደው ልጁም ባላጌነት አዋየው። ቃዲውም መልሶ «ሰው በጥሩ ሁኔታ እየሠለጠነ መልካም ነገሮች ላይ ብቻ እንዲያተኩር ሆኖ ቢያድል በሕይወት ዘመኑ መልካም ሁኔታ እንደሚያሳልፍ አንታርን ምሳሌ እያደረገ ነገረው። ትምህርት የድመትን እንኳን ባሕርይ እንደሚለውጥ አስገነዘበው።

ገበሬውም ወደ ቤቱ ተመለሰና ለብዙ ዓመታት ልጁን ማስተማር ጀመረ። ለጊዜው ሁሉም ነገር መልካም መስሎ ታየው። ነገር ግን የገበሬው ልጅ ድንገት ወደ መጥፎ ድርጊቱ በተመለሰ ጊዜ ገበሬው ተስፋ ቆረጠ፤ አዘነም።

እንደገናም ገበሬው አንድ በልዩ ሁኔታ የተጠቀለለ ኮፊዳ ይዞ ወደ ቃዲው ቤት ሄደ። የደረሰበትንም ነገር ሁሉ አጫወተው። ቃዲው ግን ከዚህ በፊት ከአጫወተው ሌላ አዲስ የሚያስተማምን ዘዴ ሊመክረው አልወደደም። በዚህ ሁኔታ ላይ ሳሉ አንታር ሻይ የተሞሉ ብርጭቆዎች በትሪ ላይ አድርጋ ከጓዳ መጣች። ገበሬው ይህን ጊዜ በእጁ ያለውን ጥቅልል ፈታና ኮሬዳውን ዘቅዘቅ ሲያደርገው ሦስት ነጫጭ አይጦች ከውስጡ ተዘረገፉ፤ አንታርም የያዘችውን ትሪ ከነብርጭቆው ወረወረችና አይጦቹን ማሳደድ ጀመረች። ብርጭቆዎቹ ተሰባበሩ፤ ሻዩም ተደፋ። ቃዲውም የዚያን ቀን «ለካስ የአንታር ባሕርይ አልተለወጠም» ሲል አሰበ።

ሽማግሌው ገበሬ ከዚህ ዓለም በሞት ከተለየ ከጥቂት ዓመታት በኋላ ከዕለታት አንድ ቀን አንድ ወጣት ገበሬ ወደ ቃዲው ቤት ሄደ። እንዴት ያለም ስድ ሰው እንደ ነበረ ነገር ግን አሁን ሕይወቱ ፈጽሞ እንደ ተለወጠ፥ ሕይወቱንም የለወጠው የእግዚአብሔር ቃል የሆነው መጽሐፍ ቅዱስ እንደሆነ ነገረው። ቃዲውም የወጣቱን ገበሬ ንግግር አደመጠ፤ በደስታ የሚያበራውን ፊቱንም ተመለከተ፤ በጉጉትም ጠየቀው፤ «ሕይወትን እንዲህ የሚለውጥ ከሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ልትሰጠን ትወዳለህን?» አለው።

በዚህ ወግ ውስጥ የሰውን ተፈጥሮና ባሕርይ እንመለከታለን። ሰው የተፈጥሮ ክፉ ባሕርዩን በሥነ-ምግባር (በግብረ-ገብ) ትምህርት

ሊለውጠው ይችላልን? «የአድርግና አታድርግ» ሕግጋት የሰውን ሕይወት ሊለውጡ ይቻላቸዋልን? ወይስ ሰው በጠቅላላው ሕይወቱን ለመለወጥ ተስፋ የሌለው ፍጡር ነው? ማንስ ሊለውጥለት ይችላል?

## «ሐላል» ወይም «ሐራም»?

(ፈታኝ ጥያቄ)

ሙስሊም ጓደኛህ የሚያስፈልገውን የምግብ ዓይነት ለመግዛት ወደ ምግብ ግሮሰሪ ይሄዳል እንበል። አንተም አብረኸው ትሄዳለህ። በዕለቱ የሚገዛው የተዘጋጀ (የቆርቆሮ) ሥጋ ነው። በግሮሰሪው ውስጥ አራት ዓይነት የሥጋ ዝግጅቶች አሉ።

1. 50% የበሬ ሥጋ እና 50% የአሣማ ሥጋ

2. 75% የበሬ ሥጋ እና 25% የአሣማ ሥጋ

3. 90% የበሬ ሥጋ እና 10% የአሣማ ሥጋ

4. 100% የበሬ ሥጋ ብቻ ይሆንና የአሳማው ሥጋ የተቀቀለበት ውኃ ብቻ ተጨምሮበታል። ሙስሊሙ የትኛውን ይመርጥ ይሆን?

ለእውነተኛው ሙስሊም አራቱም «ሐራም» ነውና ይቀምሰው ዘንድ አይሞክርም። ዝግጅቱን ሐራም የአደረገው የተቀላቀለው የአሣማ ሥጋ መጠን አይደለም፤ ጥቂትም ቢሆን መረቁ እንኳን ብቻ ቢሆን የረከሰ ነውና ይህ ለሙስሊም የተገባ አይደለም።

ኃጢአትም ቢሆን እንዲሁ ነው። የኃጢአት ትንሽ የለውምና እግዚአብሔር በኃጢአት ሁሉ የሚፈርደው ፍርድ እኩል ነው። በሰው አመለካከት ደግ ሥራ መሥራት አዎን ያገለግል ይሆናል። ለጌታ ግን 80% ወይም 50% ወይም 10% ብቻ ቢሆን ኃጢአት ለውጥ የለውም። እግዚአብሔር የሚቀበለን እርሱ ቅዱስ እንደሆነ እኛም ቅዱሳን ስንሆንለት ብቻ ነው (ማቴዎስ 5፡48፤ ዘሌዋውያን 19፡2)።

## የሁለት ሰዎች ጸሎት

(ከመጽሐፍ ቅዱስ ሉቃስ 18፡9-14)

ሁለት ሰዎች ጸሎት ለማድረስ ወደ መስጊድ ሄዱ። አንደኛው ጥሩ ሙስሊም ነበር፤ የሰላትን ሥነ-ሥርዓት በሚገባ ያውቃል፤ የዐረብኛ ቋንቋ ችሎታው መቼም እንከን አይወጣለትም፤ እንቅስቃሴው የሚናገረው ሐረግ እንደ ሙዚቃ የተስማሙ ናቸው። የብዙ ዓመት ልምምድ ያለው ሙስሊም መሆኑ ያስታውቃል። የተለመደ ጸሎቱን ሊያደርስ ወደ መስጊድ ከሄደ በኋላ ተንበርክኮ እየሰገደ ሳለ፥ አሳቡ ድንገት ተወሰደበት። ልቡን የሰረቀው ለረዥም ዓመት የጎመዠላትና ጎረቤቱ የሆነች የአንዲት ልጃገረድ ነገር ነበር።

ሁለተኛው ሰው ደግሞ በእስልምና ብዙ ያልቆየ፥ ወጣ-ገባ እያለ የሚኖር ኃጢአተኛና ኑሮውም የተበላሸበት ሰው ነበር። ሰላት እንዴት እንደሚደረግ በደንብ አያውቅም ነበርና ወደ መስጊድ መሄድ በወደደ ጊዜ ሁሉ ሙሉ ነጻነት አይሰማውም፤ የዚያን ቀን ግን ብዙ ጊዜ ማጥፋት አላስፈለገውም፤ መስጊዱ ግቢ ውስጥ ባሉት አምዶች ወደ አንደኛው ተጠጋና በራሱ ቋንቋ በዝግታ መናገር ጀመረ። «አምላክ ሆይ፥ ማረኝ፤ እኔ ሕይወቴን በገዛ እጄ አበላሽቻለሁ፤ ስለዚህም በእውነት እጸጸታለሁ፤ እንድከተለህ፥ እንዳገለግልህም እባክህ ሕይወቴን ለውጥልኝ» አለ።

| |
|---|
| በአንተ አስተሳሰብ የተኛውን ጸሎት ነው እግዚአብሔር የሚቀበለው? እግዚአብሔር የሰውን ልብ ተመልክቶ ነው የሚፈርደው። (ከማቴዎስ 23፡23-36 ጋር እያነጻጸርህ ልትጠቀምበት ትችላለህ።) |

## «የቁልፍ ልጅ»

በመሌ ቋንቋ «ቁልፍ» ለማለት «ኩትሺ»፥ መክፈቻ ለማለት ደግሞ «አና ኩትሺ» ይባላል። አና ኩትሺ ቃል በቃል ሲተረጎም «የቁልፍ ልጅ» ማለት ነው። እንዲህም ሲባል ቁልፍና ቁልፍ ተጋብተው መክፈቻውን ይወልዳሉ በማለት መሌያውያን ያስባሉ ብለህ

እንዳትገምት። መከፈቻ የሌለው ቁልፍ ዋጋ ቢስ ነው። መከፈቻ ከጠፋ ያለው አማራጭ መሰበር ይሆናል።

በተመሳሳይ ሁኔታ ዐረብ አገር ውስጥ ለጉዞ የተዘጋጀ መንገደኛ «የመንገድ ልጅ» ይባላል። ለሁላችንም ግልጽ አነጋገር ይመስለኛል። ክርስቲያኖች ግን ያለ እግዚአብሔር ልጅ ያለ ጌታ ኢየሱስ በስተቀር ነገር ሁሉ የተቆለፈ የተዘጋ እንደሆነ ያውቃሉ። እግዚአብሔር በግል ለመገናኘትም የሚያደርሰው ጎዳና ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ እንደሆነ ያውቃሉ። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ «እኔ መንገድና እውነት፥ ሕይወትም ነኝ» ያለውን አስታውስ። ያለ እርሱም በስተቀር ወደ አብ የሚመጣ ማንም እንደ ሌለ ተረዳ።

## ሞኝ ቁጥር አንድ

(ተረት)

በቤተ መንግሥቱ ውስጥ አጫዋች የነበረው አንድ ንጉሥ ነበር። ንጉሡም አጫዋቹን በጣም ስለሚወደው አንድ ቀን ልዩ ሽልማት አረገለት። ሽልማቱም የተለየ የክብር በትር ነበር። በሽልማቱም ወቅት ንጉሡ «እንደ አንተ ያለ ሞኝ (ያን ጊዜ በሚጠሩበት ስያሜ) እስከ አሁን ድረስ በቤተ መንግሥቴ ውስጥ አላየሁም። ስለዚህም ይህንን ‹የተዋንያን ልዩ በትር› ሸልሚሃለሁ። ይህ በትር ከአንተ እጅ የሚወጣው ከአንተ የበለጠ ‹ሞኝ› ቧልተኛ የአጋጠመህ እንደሆነ ብቻ ነው። ያን ጊዜ ለበለጠው ሞኝ አሳልፈህ ትሰጠዋለህ» ሲል ተናገረ።

ከዚያም በኋላ ንጉሡና አጫዋቹ በወዳጅነታቸው ጸንተው ብዙ ዓመታት አሳለፉ። በመጨረሻም ንጉሡ በማይድንበት በሽታ ታመመ። እንደ ሌሎች ሰዎች ሁሉ አጫዋቹ ንጉሥን ሊሰናበት ቀረበ። እንዲህም አለ፡- «ግርማዊ ሆይ! ወደ ሩቅ አገር እንደሚሄዱ ሰምቼአለሁ» አለ።

«አዎን ልትል ይገባሃል» መለሰ ንጉሡ።

«ለጉዞዎ የሚያስፈልግዎን ሁሉ እንደ አዘጋጁ በሚደርሱበትም አገር ታላቅ አቀባበል እንደሚደረግልዎት አልጠራጠርም።»

«አይደለም የእኔ ሞኝ! የምትለውን ሁሉ አሟልቻለሁ ለማለት እንኳ አልደፍርም።»

«ንጉሥ ሆይ! ሩቅ አገር እንደሚጓዙ አያውቁትም ኖሯልን?»

«በሚገባ እንጂ! ይህን እኮ እኔም ሌላውም ሰው ሁሉ ያውቀዋል።»

«ግርማዊ ሆይ! ጉዞዎ የማይቀር መሆኑን እያወቁ ነው ምንም አለመዘጋጀትዎ?» ... ንግግሩን ሳይቋጭ አጫዋቹ የተሸለመውንም በትር አንሥቶ በንጉሡም አልጋ ላይ አጋደመውና ቀጥሎ ያለውን ተናገረ:- «ንጉሥ ሆይ! እርስዎ የሸለሙኝን የተዋንያን በትር መመለስ ግድ ሆኖብኛል። ምክንያቱም በሕይወቴ ዘመን እንደ እርስዎ ያለ ሞኝ አላጋጠመኝምና!»

| ይህ ታሪክ አንተንም እንድታስብ፥ እንድታሰላስል ያደርግሃል። |
| --- |

## በመሠረቱ መልአኩ ገብርኤል ሊዋሽ አይችልም

### (የመጽሐፍ ቅዱስ ማጠቃለያ)

ሙስሊም ወዳጆችህ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅነት ሲሞግቱህ እንደሚከተለው ለመመለስ ሞክር:- «መላእክት የእግዚአብሔር ታማኝ መልእክተኞች እንደ ሆኑ ታውቃለህ አይደል? እንግዲህ ሉቃስ 1፡32ን እንመልከትና መልአኩ ለድንግል ማርያም የተናገረውን እንገንዘብ። ኢየሱስ «የልዑል ልጅ» እንደሚባል ይናገራል። ለመሆኑ ይህ መልአክ ማን እንደ ሆነ አስተውለሃል? አዎ፥ እርሱ መልአኩ ገብርኤል ነው (ቁጥር 26 ተመልከት)። እርሱም ለነቢዩ መሐመድ ቁርዓንን ያወረደለት የምታምነው መልአክ ነው። መልአኩ ገብርኤል ውሸት የሚናገር ይመስልሃል? በእርግጥ አይናገርም! ዳሩ ግን በዚህ ስፍራ ገብርኤል እንኳ ኢየሱስን «የልዑል እግዚአብሔር ልጅ» ብሎ ይጠራዋል። እንግዲህ መሐመድ እንኳ ከመወለዱ ከብዙ መቶ ዓመታት በፊት መልአኩ ገብርኤል ያረጋገጠውን ነገር ለማመን ለምን ትቸገራለህ?»

ይህን አሳብ ያካፈለን ወንድም እርሱ በሚኖርበት ከተማ ውስጥ የሚኖሩ ሙስሊሞች ከዚህ ምላሽ የተነሣ ሊያከብሩት እንደ ጀመሩና ብዙውን ጊዜ መልካም ውይይቶች እንዳደረጉም ጨምሮ አጫውቶናል።

# የአብርሃም ወንጌል

## የርዕሱ አስፈላጊነት

«በአብርሃም አምላክ ታምናለህን?» የሚለው ጥያቄ ሙስሊሞችን በቤታቸው ስንጎበኝ የተጠቀምንበት የመወያያ ጥያቄ ነው። ሙስሊሙ ለዚህ ቀጥተኛ መልስ አለው። «በትክክል እኔ በአብርሃም፥ በይስሐቅና በያዕቆብ አምላክ አምናለሁ። እርሱም ደግሞ የሙታን ሳይሆን የሕያዋን አምላክ ነው።»

(በገጽ 127 እና 128 ላይ ያለውን የቁርዓን ጥቅስ ተመልከት።)

## ስለ አብርሃም ስንወያይ

ሙስሊሞች አይሁዶችና ክርስቲያኖች ለአብርሃም የተለየ ክብር ይሰጣሉ፤ ለምን ይመስልሃል? የአብርሃም የተለየ ስውነት ምንድነው? ድርጊቱና ተግባሩስ ከሌሎቹ በምን ይለያል? እምነቱና ተግባሩ ለዚህ ያበቃው ይመስልሃል? ይህን ምሳሌ ተጠቀም:- ልጅ ቆጥቦ ያጠራቀመውን ገንዘብ ሁሉ ጨርሶ ለአባቱ ወይም ለእናቱ ስጦታ ሲሰጣቸው የትኛው ይበልጣል - ያወጣውን ገንዘብ ያህል የብር ቁጥር ወይስ ያሳያቸው ፍቅር?

## ወንጌልን ማቅረብ

ዓላማ:- ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች ስለ አብርሃም በሚስማሙበት ነጥብ ላይ ጀምረህ፥ አሳቡ ሲሰባሰብልህ ጥልቅ ወደ ሆነው ውይይት ትመራውና እኛ ክርስቲያኖች ስለ አብርሃም ያለንን መንፈሳዊ መረዳት ታስገነዝበዋለህ።

1. ለአብርሃም የተሰጠው የክብር ስም:- «የእግዚአብሔር ወዳጅ» (በዐረብኛ ካህሊሉላህ የሚል ነው) በመጽሐፍ ቅዱስ 2ኛ ዜና መዋዕል 20:7፤ ኢሳይያስ 41:8፤ ያዕቆብ 2:23። በቁርዓን ሱረቱ 4:125።

   ጠይቅ:- አብርሃም የእግዚአብሔር ወዳጅ ለመባል የበቃው በምንድነው? በአባባሉስ ስለ ወዳጅነታቸው ምን ያስገነዝበናል?

ማስታወሻ፡- መጠሪያው ስለ አብርሃም ስለ ራሱ ብቻ ሳይሆን ስለ አብርሃም አምላክ ደግሞ እንደሚያስረዳ አስታውስ።

* እግዚአብሔር ታማኝ አምላክ ነው። ቃል ኪዳኑን ይጠብቃል፤ እንደ ሰው ተለዋዋጭ አይደለም። ምሥጢሩንም፥ ያለውን የልቡንም አሳብ ለባሪያዎቹ ያከፍላል (አሞጽ 3፡7)። ምንኛ አስደናቂ አምላክ ነው!

2. አብርሃም በእርግጥ የእውነተኛው የእግዚአብሔር ሕዝብ ሁሉ አባት ነው። አብርሃም በዓለም ላይ ላለው ሕዝብ ሁሉ በረከት እንደሚሆን ከእግዚአብሔር የተስፋ ቃል ተሰጥቶት ነበር (ዘፍጥረት 12፡3፤ 15፡1-6፤ 17፡5፥19)። አይሁዶች እንደ አባታቸው ያዩታል (ሉቃስ 3፡8፤ ዮሐንስ 8፡33፥ 39 ከተቻለ እስከ 55 ቀጥል)።

ማንኛውም ክርስቲያን በእምነት የአብርሃም ወራሽ እንደሆነ አድርጎ ራሱን ሊቆጥር ይችላል (ሮሜ 4፡16፤ 9፡8፤ ገላትያ 3፡7 ና 8)።

ማስታወሻ፤ ዮሐንስ 8፡56 ና ገላትያ 3፡8 በጣም ድንቅ አባባሎች ናቸው። አብርሃም ክርስቶስን ለማየት ናፍቆአል፤ አስቀድሞ ወንጌሉንም ተቀብሎአል። ይህን ነጥብ በደንብ ለማብራራት ሞክር።

ቁርዓን አብርሃም ለሰዎች ሁሉ ምሳሌ የሚሆን መሪ መሆኑን ይናገራል (ሱረቱ 2፡124፤ 16፡120፤ 3፡67)። አብርሃም አይሁድም ክርስቲያንም አልነበረም፤ ነገር ግን በእምነቱ እውነተኛ ነበር።

* ይህ የመጨረሻው ነጥብ መኖሩን እወቅ፤ ነገር ግን አንተ ራስህ ባታነሣው ይመረጣል።

3. አብርሃም በጌታ ፊት ሞገስ ያገኘው በእምነቱ ብቻ ነው። ሙስሊሞች የአብርሃምን የእምነት መንገድ እንዲከተሉ ይበረታታሉ (ሱረቱ 3፡95፤ 2፡135፤ 6፡161)።

ክርስቲያኖችም የአብርሃምን እምነት እንድናስተውል ታዘናል (ገላትያ 3፡6-9)።

ምሳሌ፤ ለማዳ ውሻ አይተህ ታውቃለህ። ውሻው አሳዳጊው እንዳስተማረው ሲያዘው ትዕዛዙን ይፈጽማል። «ተቀመጥ» ሲለው

ይቀመጣል፤ «ተነሥ» ሲለው ይነሣል። ውሻው ግን ይህን ሁሉ ስለ አከናወነ በአሳዳጊው ላይ እምነት አለው ለማለት አይቻለንም። ብቻ የተባለውን እንዲታዘዝ ሠልጥኗል። ታዛዥነት ሁልጊዜ ከትዕዛዝ ጋር የተቆራኘ ነገር ነው። ነገር ግን እምነት አይባልም። ወይም መታመንን አያሳይም። የአብርሃም እምነት የእግዚአብሔር የታማኝነቱ ነጸብራቅ ነው (1ኛ ቆሮንቶስ 10፡13፤ 2ኛ ተሰሎንቄ 3፡3)፤ እምነቱም ጽድቅ ሆኖ ተቆጠረለት (ዘፍጥረት 15፡6)።

4. የአብርሃም የቃል ኪዳን ልጅ

ይኼኛው ነጥብ በመጽሐፍ ቅዱስም በቁርዓንም ተገልጿል፤

«ሚስቱም የቆመች ስትኾን (አትፍራ አሉት) ሳቀችም፤ በኢስሐቅም አበሰርናት» (ሱረቱ 11፡71)። የቃል ኪዳን ልጁ እስማኤል ሳይሆን ይስሐቅ መሆኑን አስታውስ (ሱረቱ 37፡112)።

በመጽሐፍ ቅዱስ በዘፍጥረት 17፡15፥ 16፥ 19 ያትተዋል።

ማስታወሻ፤ አብርሃም እግዚአብሔር ከተናገረ የተናገረውን እንደሚፈጽም ያምን ነበር (ሮሜ 4፡18-22፤ ዕብራውያን 11፡11፤ ምሳሌ 30፡5)።

5. ልጁን እንዲሠዋ አብርሃም ስለ መታዘዙ

ስለዚህ ነጥብ በሱረቱ 37፡102-113 የተጻፈው ሁኔታ መጽሐፍ ቅዱስ ከሚለው በጣም የተለየ ነው። መቼም አብርሃም «እንዲህ ያለ ቅዱስ አምላክ ልጁን ሠዋልኝ ብሎ ለማዘዝ ሕሊናው እሺ ይለዋልን?» የሚል ጥያቄ በአእምሮው ውስጥ ሊፈጠር ይችል ይሆናል። አላህ ለሚያዘው ነገር ሁሉ ግን አይጠየቅም!

አባባሉን ከዘፍጥረት 22፡1-13 ከተጠቀሰው ምንባብ ጋር አነጻጽረው። አብርሃም በእርግጥ ደንግጦ ይሆናል በትዕዛዙ፤ ነገር ግን በእምነት ታዘዘ፤ በኋላም የእግዚአብሔርን የማዳኑን ምሥጢር ተረዳ። ባለ ሦስት ፊት ፈተና ነበር፡-

1. የእግዚአብሔርን ፍቅር እንዲያሳይ

2. እምነቱን በእግዚአብሔር ላይ እንዲያደርግ

3. በእምነቱም እንዲጸና

አብርሃም እግዚአብሔርን የሚጠይቅ የሚከራከርም ሰው ነበር (ዘፍጥረት 18፡23-28)። ምናልባት ከእነዚህ አራቱ ነጥቦች ምክንያት ይሆናል፡-

1. እግዚአብሔር ቃል ኪዳኑን ረስቶታል

2. እግዚአብሔር አሳቡን ለውጧል

3. ያለ ጥያቄ ዝም ብዬ እንድታዘዝለት ይፈልጋል

4. በኋላ ግን እግዚአብሔር ቃሉን መፈጸሙ አይቀርም

ለአብርሃም የቀረው ተስፋ አንድ ብቻ ነበር። «እግዚአብሔር ልጄን ከሙታንም እንኳን ቢሆን ያስነሣዋል» (ዕብራውያን 11፡17-19)። እስቲ አባባሉን ከሱረቱ 2፡260 ጋር እነጻጽረው። የአብርሃም እምነት እንዲህ ነበር!

«ኢብራሂምም ጌታዬ ሆይ! ሙታንን እንዴት ሕያው እንደምታደርግ አሳየኝ ባለ ጊዜ . . . አላመንክምን? አለው፤ አይደለም (አምኛለሁ)፤ ግን ልቤ እንዲረጋ ነው አለ።»

አስታውስ፤

አብርሃም አስቀድሞ ወንጌልን በእምነቱ አይቶታል። የሚወደው ልጁ፡-

- ባልተለመደ ሁኔታ የተወለደ ነው

- ለኃጢአት መሥዋዕት ሊሠዋም ነበር

- ከሞት መነሣቱ

- ለአሕዛብ ሁሉ በረከት መሆኑ

ስለዚህም ይስሐቅ የእግዚአብሔር የማስታረቅ ሥራው ሕያው ምሳሌአችን ነው።

የማጠቃለያ ጥያቄዎች፡-

1. እግዚአብሔር እንደ ወደደህ በምን ታውቃለህ? ስለ ወደደህ ምን አደረገልህ?

2. እግዚአብሔር የአብርሃምን ምሳሌነት የሚመስል ሥራ ሠርቶ ያውቃልን?

3. ሰው ለእግዚአብሔር ያለውን ፍቅር አንድያ ልጁን በመስጠት መግለጽ ከቻለ፥ እግዚአብሔርስ እንዴት ባለ መንገድ ነው ለእኛ ያለውን ፍቅር የሚገልጸው?

አስታውስ፡- እግዚአብሔር ለሰው ሊያደርግ ከሚፈቅደው በላይ ሰው እንዲያደርግለት አይጠይቀውም ... የበለጠውን ነገር እንደሚጠይቅ በፍጹም አይታሰብም!

## አብርሃም በቁርዓን ውስጥ

### ሱረቱ

| | |
|---|---|
| 2፡124 | - እግዚአብሔርን ታዘዘ |
| 2፡125 | - ከዓባ (3፡96-97) |
| 2፡130-135 | - የአብርሃምን ሃይማኖት መከተል |
| 2፡258 | - ከማያምኑ ሰዎች ጋር ይከራከር ነበር |
| 2፡260 | - ለሙታን ሕይወት የሚሰጥ እግዚአብሔር መሆኑን ያምናል |
| 3፡67 | - አይሁድም፥ ክርስቲያንም አልነበረም |
| 3፡95 | - አረመኔም አልነበረም |
| 6፡74 | - ጣዖታትን ተከራከረ (19፡41-50) |
| 6፡75-79 | - የሰማይ ፍጥረታትን እንዳያመልኩ ተቃወመ |
| 6፡80-83 | - ሕዝቡን ሰበከ |
| 9፡113-114 | - ስለ አባቱ ማለደ (26፡86) |

| | |
|---|---|
| 11፡69-73 | - ወደ ሉጥ የሚሄዱትን መልእክተኞች ለመን |
| 14፡35-41 | - የአብርሃም ጸሎት (26፡83-87) |
| 16፡120-123 | - ምሳሌ ሆነ |
| 21፡51-71 | - የጣዖት አምልኮን ተቃወመ (26፡70-82፤ 29፡16-18፤ 37፡83-98) |
| 21፡69 | - እሳት አይበላውም |
| 37፡99-111 | - ልጁን ሠዋ |
| 53፡37 | - የአብርሃም መጽሐፍ (87፡19) |
| 60፡4-6 | - ከማያምኑት ጋር ሲሆን ያለው ምሳሌነት። |